# የአስተዳደር ዘርፍ
# የሙስና መከላከል እና ሥነ-ምግባር ግንባታ

## (ማሰልጠኛ ሞጁል)

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

— ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ —

CORRUPTION FREE ETHIOPIA

ህዳር 2017 ዓ.ም
አዲስ አበባ
ኢትዮጵያ

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS & ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ከሙስና የጸዳች ኢትዮጵያ
CORRUPTION FREE ETHIOPIA

# የአስተዳደር ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

# (የሥልጠና ሞጁል)

ህዳር 2017 ዓ.ም

አዲስ ኣበባ

ኢትዮጵያ

# የአስተዳደር ዘርፍ የሙስና መከላከል እና ሥነምግባር ግንባታ

# የሥልጠና ሞጁል)


አዘጋጆች፡-

ዶ/ር በረከት ሰለሞን

ዶ/ር መሀመድ ይማም

አርታኢ፡-

አቶ ሀረጎት አብርሃ

አቶ የኒላሸት ደሳለኝ

አቶ ቤዛ በኃይሉ

አቶ አንተነህ ሀይሌ

ግራፊክስ ዲዛይን፡-

አቶ በለጠ ብርሀኑ



© የፌደራል የሥነ-ምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን



ህዳር 2017 ዓ.ም

# ማውጫ


ማውጫ ..... 4
መግቢያ ..... 6
1. የሞጁሉ ዓላማዎች ..... 9
1.1 የሞጁሉ ዋና ዓላማ ..... 9
1.2 የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች ..... 9
2. የሚጠበቁ ውጤቶች ..... 9
3. የሥልጠናው ሥነ-ዘዴ ..... 10
4. ስልጠናው በአጠቃላይ የሚወስደው ጊዜ ..... 10
ምዕራፍ አንድ፡ የሙስና ምንነት፣ የሙስና ወንጀሎችና መገለጫዎች ..... 11
1.1 የምዕራፍ አንድ መግቢያ ..... 11
1.2 የምዕራፍ አንድ አላማዎች ..... 11
1.3 የተፈቀሰው ሰዓት ፡- 2፡00 ሰዓት ..... 11
1.4 የማሰልጠኛ ዘዴዎች ..... 11
1.5 የሙስና ወንጀል ምንነት? ..... 12
1.6 የሙስና ዓይነቶች ..... 14
1.6.1 ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption) ..... 14
1.6.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption) ..... 15
1.6.3 ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture) ..... 16
1.6.4 ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption) ..... 16
1.7 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት ..... 16
1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች ..... 19
ማጠቃለያ ..... 28
ምዕራፍ ሁለት፡ የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት፣ስጋትና ብልሹ አሰራሮች ..... 29
2.1 የምዕራፍ ሁለት መግቢያ ..... 29
2.2 የምዕራፍ ሁለት ዓላማዎች ..... 29
2.3 የሙስና ተጋላጭነት ምንነት እና ምክንያቶች ..... 29
2.4 በአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሙስና ተጋላጭነት እና ብልሹ አሰራሮች ..... 30
2.4.1 የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት ..... 30
2.4.2 ተጠያቂነትን ማስፈን ..... 32

2.4.3 የተቋማት ግልፅነት ........ 33
2.4.4 አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ ........ 34
2.4.5 የንብረት አስተዳደር ........ 35
2.4.6 የግዥ አስተዳደር ........ 36
2.4.7 የሰው ሀብት አስተዳደር ........ 37
2.4.8 የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ ........ 38
2.4.9 የፕሮጀክቶች አስተዳደር ........ 39
2.4.10 የኦዲትና ቁጥጥር ........ 40
2.4.11 የግል ጥቅም የሚያጓጓቸው ሀላፊዎች መበራከት ........ 41
2.4 በአስተዳደር ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች ........ 42
2.5.1 የባንክ አገልግሎት አሰጣጥ ብልሽት ........ 42
2.5.2 ፓስፖርት አሰጣጥ ጉዳይ ........ 43
2.5.3 የተንዛዛ አሰራር ........ 44
2.5.4 በቂ ያልሆነ ቁጥጥር እና ተጠያቂነት ........ 45
2.5.5 ፖለቲካዊ ተጽእኖ እና በትዉዉቅ የሚሰሩ ስራዎች ........ 46
የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ........ 46
የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች ........ 47
ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች ........ 48
ምዕራፍ ሶስት፦ በአስተዳደር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች ........ 49
3.1 የምዕራፍ ሶስት መግቢያ ........ 49
3.2 የምዕራፍ ሶስት ዓላማዎች ........ 50
3.3 በአስተዳደር ዘርፍ ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች ........ 50
3.4 በዘርፉ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ መንገዶች እና ስልቶች ........ 55
3.5 ማጠቃለያ ........ 60
ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች ........ 61
አባሪ 1፦- ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት ........ 63
ቅድመ ስልጠና መገምገሚያ ቼክ ሊስት ........ 63
ድህረ ስልጠና መገምገሚያ ቼክ ሊስት ........ 64
አባሪ 2: በዘርፉ የተገኙ ኬዞች ........ 66
ዋቢ መጽሐፍት / References ........ 70

## መግቢያ

ሙስና መገለጫው ዘርፈ ብዙ እንዲሁም ጉዳቱም ዘርፈ ብዙ ወንጀል ነው፡፡ በሃገር ሁለንተናዊ እድገት ላይ አሉታዊ ተፅእኖ የሚያስከትል እና ማህራዊ ምስቅልቅል የሚያመጣ የልማት ጠንቅ ነው፡፡ ሙስና የህዝብ አለመተማመንን የሚፈጥር እና ዋናዋና ተግባራትን እና ተልዕኮዎችን የመፈጸም ድርጅታዊ አቅምን ያዳክማል፡፡ ሙስና በመንግስት አሰራር ላይ ጣልቃ በገባ ቁጥር የአሰራር እና የፍትህ መዛባት ያስክትላል፤ማህብራዊ ቀውስም ይፈጥራል፡፡

የሙስና ወንጀል አደገኛነቱ በሚስጥርና በጥንቃቄ የሚፈጸም መሆኑ ነዉ፡፡ በዚህም ምክንያት መፈጸሙን ለማወቅ የሚያስችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት ሊያስቸግር ይችላል፡፡ ሙሰኞች የሚሰሩት ስራ ወንጀል መሆኑን ስለሚያውቁ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል አሻራ እንዳይገኝ ያጠፋሉ፡፡ ሙስና ማህበራዊ ሞራል መሸርሸርን ፖለቲካዊ ልሽቅናን ያመልክታል፤ውጤቱም ሀገርን እና ህዝብን ማውደም ነው፡፡

ጥናቶች እንድሚያሳዩት ሙስና በሀገራችን ላይ ኑሮ ውድነትን ከማባባስ፣ ኢኮኖሚያዊ፣ ማኅበራዊና ፖለቲካዊ እድገቶችን በመግታት ረገድ ከፍተኛ እንቅፋት እየፈጠረ የሚገኝ ከባድ ወንጀል ነው፡፡ ይህ ወንጀል ከጊዜ ወደ ጊዜ መልኩን፣ ጸባዩንና የአፈጻጸም ሥልቱን እየቀያየረ በመንግሥታዊ ተቋማትና መንግሥታዊ ያልሆኑ ድርጅቶች ላይ በተለያዩ ተሳታፊ አካላት እየተፈጸመ ነው፡፡

ሙስናን የመከላከል ሃላፊነት ያለባቸው አካላት እና ተቋማት ሁልጊዜ ትኩረታቸው የሙስና ጠቋሚ ሁኔታዎች ላይ እንዲሆን ይመከራል፡፡ ምክንያቱም ሳይቃጠለ በቅጠል እንዲሉ ሙስና ተከስቶ ብዙ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አንቂ ወይም አስጠንቃቂ ምልክቶችን አይቶ የመከላከል ስራ መስራት ከብዙ ጥፋት ወይም ጉዳት ያድናልና፡፡ ከሁሉም በላይ የዜጎችን አተያይ ማከም እና ማስትካከል ያስፈልጋል፡፡ ዜጎች ሙስና ማህበራዊ፣ባህላዊ እና ፖለቲካዊ በሽታ ስለሆነ አእንደማንኛውም በሽታ እንዳይዛቸው እንዲጠነቀቁት ማስተማር እና ማስጠንቀቅ ያስፈልጋል፡፡

በርካታ በማደግ ላይ ያሉ ሀገራት ሙስናና ብሉሹ አሰራርን በመዋጋት ለዜጎች ፍትሀዊ አገልግሎት ለመስጠት ከፍተኛ ጥረት በማድረግ ላይ ናቸው፡፡ ሙስናና እና ብልሹ አሰራር በሀገርና በዜጎች ላይ ያለውን አሉታዊ ተጽዕኖ በመረዳት የኢትዮጵያ ፌደራላዊ ዲሞክራሲ መንግስት (ኢፌዲሪ) በርካታ ፖሊሲዎችንና ስታራቴጂዎችንን በመቅረጽ አበረታች ተግባራትን ሲያከናውን ቆይቷል፡፡

በተለይ ደግሞ ከለውጡ በኂላ መንግስት ሙስናንና ሌብነትን በመጸየፍ የተጠናከረ እርምጃ በመውሰድ ላይ ይገኛል፡፡

በ 2015 የሥነምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ያስጠናው ጥናት እንዳመለከተው ሁሉም የመንግስት ቢሮዎች ለሙሰና ተጋላጭ የመሆናቸው እድል ሰፊ መሆኑ ነው፡፡ በመሆኑም በተለመደው መንግድ ሙስናን መዋጋት ውጤት እንደማያመጣ የተረዳው ኮሚሽኑ ዘርፍ ተኮር ሙስናን የመከላክል መንገድ እየተከተለ ነው፡፡ ሰርቆ መበልጸግ እንደ ጀግንነት የሚቆጠርበት አስፈሪ ዘመን ላይ እየደርስን ስለሆነ ዘርፍ ተኮር የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ማዘጋጀትና ተግባራዊ ማድረግ ከመቼውም ጊዜ በላይ አስፈላጊ ሆኗል፡፡

ሙስናና ብልሹ አሰራርን መዋጋት የሁሉም ዜጋ ኃላፊነት መሆኑ የሚታወቅ ቢሆንም በመንግስት አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ላይ ያሉ ሠራተኞች ደገሞ የአንበሳውን ድርሻ ይወስዳሉ፡፡ ዜጎች አገልግሎት ለማግኘት ወደ መንግስት ተቋማት በሚሄዱበት ወቅት የተቀላጠፈ፣ ግልጽና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት ማግኘት ይፈልጋሉ፡፡ ሠራተኞች ደግሞ የተጣለባቸውን ሙያዊና ሀገራዊ ድርብ ኃላፊነትና ግዴታ ከግምት በማስገባት ለዜጎች ሙያዊ ስነ-ምግባርን በመላበስ ፍትሀዊና ከሙስና የጸዳ አገልግሎት መስጠት ይጠበቅባቸዋል፡፡

ይሁን እንጂ ይህንን ለማሳካት ሠራኞች ተከታታይ የሆነ የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና እንደሚያስፈልጋቸው እሙን ነው፡፡ ይህንንም ከግንዛቤ በማስገባት የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ባለፉት ዓመታት በርካታ ስራዎችን ሲሰራ የቆየ ሲሆን በዚህም አበረታች ለውጦች እየታዩ ነው፡፡ የፌደራል ሥነምግባርና የፀረ መስና ኮሚሽን በአዋጅ ቁጥር 1236/2021 በተሰጠው ሥልጣን መሰረት በመንግስት መስሪያ ቤቶች፣ በመንግስት የልማት ድርጅቶች እና በህዝባዊ ድርጅቶች የሚሾሙ ወይም የሚመደቡ ወይም የሚቀጠሩ የስራ ኃላፊዎች እና ሰራተኞች የሥነ-ምግባር እና የሙስና መከላከል ስልጠና በመስጠት ሰራተኞች እና የስራ ኃላፊዎች የራሳቸውንና የተቋማቸውን ሥነ ምግባር እንዲገነቡ እና በተቋማቸው ውስጥ ያለውን ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አኳያ ያሉትን ክፍተቶች እንዲሞሉ የማድረግ ኃላፊነት አለበት

ይህንንም መነሻ በማድረግ ቀደም ሲል የተጀመሩ ስራዎችን በይበልጥ በማጠናከር ኮሚሽኑ በ2017 የበጀት ዓመት በሀገሪቱ ካሉ ነባር ዩኒቨርሲቲዎች ተባባሪ አሰልጣኞችን የመለየት ስራ ያከናወነ ሲሆን ከተመረጡ ምሁራኖች ጋር በመቀናጀት ተከታታይ የሆነ ዘርፍ ተኮር የሆኑ የሙስናና

ብልሹ አሰራሮችን የመከላከል የግንዛቤ ማስጨበጫ ሥልጠና ለመስጠት ማቀዱን መነሻ በማድረግ ይህ የሥልጠና ሞጁል ሊዘጋጅ ችሏል፡፡

እንደሚታወቀው የአስተዳደር ዘርፍ ማለት በጠቅላይ ሚኒስተር ጽ/ቤት ስር ተጠሪ የሆኑ በርካታ ተቋማትን የያዘ ሲሆን እንዚህ ተቋማትም በአንድም ሆነ በሌላ መንገድ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ናቸው፡፡ በአስተዳደር ዘርፍ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ወደ 18 የሚደርሱ ተቋማት ተጠሪ የሆኑ ሲሆን ከእነዚህም ተቋማት መካከል ሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የመረጃ መረብና ደህንነት አስተዳደር፣ የፋይናንስ ደህንነት አገልግሎት፣ የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩት፣ እንዲሁም የብሔራዊ መረጃ ደህንነት አገልግሎት በዋናነት ይጠቀሳሉ፡፡

ለምሳሌ ያህል የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከሠራተኛ ቅጥር፣ምደባና ዝውውር አፈጻጸም ጋር በተያያዘ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊሆን ይችላል፡፡ የኢትዮጵያ ስራ አመራር ኢንስቲትዩትንና የአፍሪካ አመራር ልህቀት አካዳሚን ብንወስድ ከስልጠና አሰጣጥ እንዲሁም ከማማከርና ምርምር ስራዎች ጋር በተያያዘ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ የመሆን ዕድል ሰፊ ነው፡፡ የፋይናንስ ደህንነት አስተዳደር ከገንዘብ ዝውውር ጋር በተያያዘ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ሊሆን ይችላል፡፡

በዚህም መነሻነት በአስተዳደር ዘርፍ ያሉ ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር የመጋለጥ እድላቸው ከፍተኛ መሆኑን ከግንዛቤ በማስገባት ይህን ሞጁል ማዘጋጀት አስፈላጊ ሆኗል፡፡ በመሆኑም ይህ የሥልጠና ሞጁል በዋናነት በአስተዳር ዘርፍ የሚታዩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን፣ የሚያስከትሉትን ጉዳት እንዲሁም የመከላከያ ዘዴዎችን የያዘ ነው፡፡ ሞጁሉ በተጨማሪም የሞጁሉን ዋና እና ዝርዝር ዓላማዎች እና የሚጠበቁ ውጤቶችን ይዟል፡፡

# 1. የሞጁሉ ዓላማዎች

## 1.1 የሞጁሉ ዋና ዓላማ

የዚህ ስልጠና ዋና ዓለማ በአስተዳደር ዘርፍ ባሉ ተቋማት የሚሰሩ ሠራተኞች ተገቢውን እውቀት፣ ክህሎት እና አመለካከትን በመገንባት በዘርፉ የሚያጋጥመውን ሙስናና ብልሹ አሰራር እንዲከላከሉ ማደርግ ነው፡፡

## 1.2 የሞጁሉ ዝርዝር ዓላማዎች

ሰልጣኞች ከዚህ ሞጁል ስልጠና በኋላ፤

- የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎች ይዘረዝራሉ፤
- የአስተዳደር ዘርፍ ለሙስና ያለውን ተጋላጭነት ይለያሉ
- በአስተዳደር ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ የሚስተዋሉ ዋና ዋና ሙስናና ብልሹ አስራሮችን ይተነትናሉ፣
- በአስተዳደር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትል የሚችሉትን ጉዳት ይለያሉ፣
- በአስተዳር ዘርፍ የሚፈፀሙ የሙስና ተግባራት መከላከያ መንገዶችን ይዘረዝራሉ ወይም ይለያሉ፡፡

# 2. የሚጠበቁ ውጤቶች

ከዚህ ሥልጠና ሞጁል ትግበራ በኋላ በዋናነት የሚጠበቁ ውጤቶች የሚከተሉት ናቸው፡

- ሠልጣኞች በሙስና ወንጀሎች ምንነት ላይ በቂ ግንዛቤ በማግኘት ለሌሎች ያሳውቃሉ
- ዘርፉ ለሙስና ያለው ተጋላጭነት እና የሚስተዋሉ ዋና ዋና ሙስናና እና ብልሹ አሰራሮች ላይ በቂ ግንዛቤ በማገኘት መከላከል የሚያስችል ብቃት ይኖራቸዋል
- ሠልጣኞች በዘርፉ የሚታዩ መስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉ ጎዳቶችን በመለየት የመከላከያ መንገዶች ላይ በቂ ግንዛቤ እና ክህሎት በማግኘት የመከላከል አቅም ያጎለብታሉ።

## 3. የሥልጠናው ሥነ-ዘዴ

የመወያያ መልመጃዎችንና ተግባራትን በማቅረብ የሚከተለት ዋና ዋና ዜዴዎችን ይጠቀማሉ፡፡

- የቡድን ወይይት (Group discussion)
- ሀሳብ የማፍለቅ ተግባር (Brainstorming Sessions)
- ገለጻ (Presentations)
- ኬዝ ጥናት (Case studies) ዘዴዎችን ያጠቃልላል፡፡

## 4. ስልጠናው በአጠቃላይ የሚወስደው ጊዜ

ይህ ስልጠና በአስተዳደር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን መከላከያ ስልቶችን በተመለከተ ሲሆን ዘርፉ እጅግ በጣም ሰፊና በርካታ ተቋማትን በውስጡ ያቀፈ ነው፡፡ ይሁንና ሞጁሉ በሶስት ምዕራፎች የተከፈለ መሆኑን ከግምት በማስገባት እና ሠልጣኞች በቀን ለ 8 ሰዓት ስልጠናው እንዲወስዱ በማድረግ በአጠቃላይ ለስልጠናው የሚያስፈልገው ጊዜ 12 ሰዓት ነው፡፡ ስለዚህ የመጀመሪያውን ምዕራፍ ለማሰልጠን 2፡00 ሰዓት እንዲሁም ሁለተኛውን ምዕራፍ ለማሰልጠን 6፡00 ሰዓት እና የመጨረሻውን ምዕራፍ ለማሰልጠን 4፡00 ሰዓት የሚፈጅ ይሆናል ፡፡

# ምዕራፍ አንድ፦ የሙስና ምንነት፣ የሙስና ወንጀሎችና መገለጫዎች

## 1.1 የምዕራፍ አንድ መግቢያ

የሙስና መከላከል ስራን በተጨባጭ ለመስራት ስለሙስና ወንጀል ምንነት አስቀድሞ መረዳት ተገቢ ነው፤ ምክንያቱም ብዙ ሰዎች የሙስና ወንጀልን ከጉቦ መስጠትና መቀበል ጋር ብቻ አያይዘው ስለሚረዱት ነው፡፡ ይሁንና ለሙስና ምንነት አንድ አለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት ባይቻልም የሙስና ወንጀል መገለጫዎችን ግን ዘርዝሮ ማየት ይቻላል፡፡ በመሆኑም ሰልጣኞች በሙስና መከላከል ዙሪያ ተገቢውን እውቀትና ክህሎት እንዲያገኙ ይህ ምዕራፍ የሙስና ወንጀል ምንነትና መገለጫዎችን የሚቀርብበት ምዕራፍ ነው፡፡

## 1.2 የምዕራፍ አንድ አላማዎች

የዚህ ምዕራፍ ዋና አላማ ሰልጣኞች ከአስተዳደር ዘርፍ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር በሙስና ምንነት፣ የሙስና ወንጅሎች ልዩ ባህሪያት የሙስና ወንጅል አይነቶች እና መገለጫ መንገዶች ላይ ያላቸውን እውቀት፣አመለካከት እና ግንዛቤ በማጎልበት ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲከላከሉ ማስቻል ነው።

ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ ሰልጣኞች ፤

- የሙስና ወንጀል ምንነትን ይለያሉ፤
- በሀገራችን ያሉትን የሙስና ወንጀሎች መገለጫዎችን ይዘረዝራሉ፤

## 1.3 የተፈቀሰው ሰዓት ፡- 2፡00 ሰዓት

## 1.4 የማሰልጠኛ ዘዴዎች

የአእምሮን ጓዳ ማንኳኳት /Brain storming/፣ገለፃ፣ ጥያቄና መልስ፣ ውይይት፣አስረጅ ናሙና (case study)

**መርጃ መሳሪያዎች፡-** ፍሊፐ ቻርት፣ማርከር፣ፓወር ፖይንት፣ የተዘጋጀ ሰነድ

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ካለው ተሳታፊ ጋር ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤

1. ሙስና ምንድነው?
2. መገለጫዎቹስ፣እንዴትስ ይፈጸማል?
3. ከጉቦ ውጭ የምታውቁትን የሙስና ወንጀል ዓይነቶችን ዘርዝሩ
4. ሙስና ማለት ሌብነት ነው በሚለው ሃሳብ መስማማት አለመስማማታችሁን አስረዱ።

## 1.5 የሙስና ወንጀል ምንነት?

ሙስና እንደየ ሀገሩ ተጨባጭ ሁኔታ፣ የሰው ልጅ ስልጣኔ እና ስርዓት በተለያየ መንገድ መጠንና አይነት የሚከሰት በመሆኑ አንድ ወጥና በሁሉም ዘንድ ተቀባይነት ያለው ትርጉም ማግኘት ያስቸግራል። እንዲሁም ሙስና ሰው ሰራሽ ድርጊት/ወንጀል/ በመሆኑ ከሰው ልጆች ባህል፣ እሴት፣ የአኗኗር ዘይቤ፣ የስልጣኔ ደረጃ ወዘተ ጋር አብሮ የሚለወጥና የሚቀያየር በመሆኑ ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

ለምሳሌ በአንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ጉቦ የሚቆጠር ድርጊት በሌላው ማህበረሰብ እንደ ስጦታ ሊቆጠር ይችላል። እንዲሁም አንድ የፖለቲካ አመራር ወይም ኃላፊ ለቤተሰቡ፣ለጓደኞቹ ለፓርቲ ደጋፊዎቹ ከሥራው ጋር በተያያዘ ድጋፍ ቢያደርግ በአንዳንድ ማህበረሰብ ውስጥ እንደ ትክክለኛ ተግባር ሲወሰድ በሌላው ማህበረሰብ የሙስና ወንጀል ይሆናል (World Bank 2006) ።

ከዚህ የተነሳ ብዙዎቻችን ስለ ሙስና ምንነት ግንዛቤ ቢኖረንም የሁላችንም ግንዛቤ ሙሉ ለሙሉ ተመሳሳይ ላይሆን ይችላል ማለት ነው። ለዚህም ነው በመጀመሪያ ስለ ሙስና ምንነት መነጋገር የሚያስፈልገው። በመሆኑም በዚህ ትምህርት ውስጥ ለሙስና የተሰጡትን ትርጉሞች እንመለከታለን ።

የሙስናን ትርጉም በዝርዝር ከማየታችን በፊት ሰልጣኞች ያላቸውን ግንዛቤ ለመፈተሽ እንዲያስችል ከዚህ በታች መልመጃ አንድ የቀረቡ ጉዳዮችን በቅድሚያ እንስራ

በአጠቃላይ ሙስና የሚለዉ ቃል የሚያስተላልፈዉን ትርጉም በተገቢዉ ደረጃ ተገንዘቦ አንድ ሊያስማማ የሚችል ሁሉን አቀፍ የሕግ ትርጉም ማግኘት በጣም አስቸጋሪ ሆኖ ቆይቷል፡፡ ትራንስፓረንሲ ኢንተርናሽናል (Transparency International) የተባለ ተቋም "ሙስና" የሚለዉን ቃል ሲፈታዉ እንዲህ ይላል፡፡ corruption is Defined as "Misuse of Entrusted Power for Private Gain." በዚህ ትርጉም መሰረት "ሙስና ማለት በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ ለግል ጥቅም ማዋል" ነዉ የሚል ሲሆን ከዚህ መረዳት የሚቻለዉ በአደራ የተሰጠን ሥልጣን አላግባብ በመገልገል ጉዳይን አላግባብ ማጓተት ወይም አላግባብ ፈቃድ በመስጠትና በማጽደቅ ጉቦ ወይም የማይገባ ጥቅም መቀበል በሙስና ወንጀል እንደሚያስጠይቅ ይገልጻል፡፡

ሙስና የእንግሊዝኛውን "Corruption" የሚለውን ቃል እንዲገለጽ የምንጠቀምበት ከግእዝ የተወሰደ ቃል ነው፡፡ ለሙስና ወጥ የሆነ ትርጉም ለመስጠት አስቸጋሪ ነው፡፡ በመሆኑም የተባበሩት መንግስታት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ የአፍሪካ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን፣ በአውሮፓ ህብረት የፀረ- ሙስና ኮንቬንሽን እና የኢትዮጵያ የሙስና ወንጀልች ህግ፣ የፀረ-ሙስና ህጎችን ብንመረምር ለሙስና ትርጉም ከመስጠት ይልቅ የሙስና ወንጀሎች የሚባሉትን መዘርዘር ላይ ትኩረት አድርገዋል፡፡

ከዚህ አኳያ የፀረ-ሙስና ልዩ የሥነ-ሥርዓትና ማስረጃ ሕግ አዋጅ ቁጥር 236/1993 ለመጀመሪያ ጊዜ ለሙስና ወንጀል ትርጉም የሰጠና በወቅቱ በስራ ላይ በነበረዉ የ1949 የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ ዉስጥ ከሚገኙ የወንጀል ድንጋጌዎች መካከል የሙስና ወንጀል ሊባሉ የሚችሉትን ያስቀመጠ ህግ ነበር፡፡ በዚሁ አዋጅ አንቀጽ 2(1) ለሙስና ወንጀል የተሰጠዉ ትርጓሜ የሚከተለዉን ይመስላል፤

የሙስና ወንጀል ማለት ከመንግስት ወይም ከህዝብ አገልግሎት ወይም ከህዝብ ጥቅም ጋር በተያያዘ የሚፈጸም ማናቸዉም ወንጀል ሆኖ የተመደበበትን የመንግስት ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራ ያለአግባብ በመጠቀም ለራስ ወይም ለሌላ ሰዉ ወይም ቡድን ጥቅም መጠየቅ፣ የተስፋ ቃል መቀበል ወይም ማግኘት ወይም ሌላዉን ሰዉ መጉዳት ሲሆን መደለያ መቀበልን፣ ጉቦን፣ የማይገባ ጥቅም መቀበልን፣በስልጣን መነገድን፣ በስልጣን ያለአግባብ መገልገልን፣ የመንግስት ስራ ወይም የህዝብ አገልግሎት ስራን ለግል ጥቅም በሚያመች አኳኋን መምራትን፣ በስራ ተግባር ላይ የሚፈጸም መዉሰድና መሰወርን፣በመንግስት ስራ ላይ ሆኖ በማስገደድ

መጠቀምን፣ሚስጥር ማባከንን እና የመሳሳሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል“ የሚል ትርጉም ተሰጥቶት ነበር፡፡

ሆኖም በዚህ አዋጅ ለሙስና ወንጀሎች የተሰጠዉ ትርጉም የተወሰኑ የሙስና ወንጀል የሚሆኑ የወንጀል አይነቶችን የዘረዘረ ቢሆንም ጉቦ መስጠትና ማቀባበል ፣ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ይዞ መገኘት፣ በወንጀል ድርጊት የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና የመሳሰሉትን የሙስና ወንጀሎች የማያካትት ከመሆኑም በላይ *“... የመሳሰሉትን ሌሎች ጉዳዮች ይጨምራል...”* በሚል የተቀመጠዉ ሀረግ በክስ አቀራረብና ዉሳኔ አሰጣጥ ላይ መቋጫ የሌለዉ የትርጉም ልዩነት በዳኞች ፣በዓቃቤ ህጎች እና በጠበቆች መካከል እንዲፈጠር አድርጎ ነበር፡፡

የ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ሲወጣ የቀድሞዉን የወንጀለኛ መቅጫ ሕግ እና ልዩ የወንጀለኛ መቅጫ ሕጉን በግልጽ ሽሯል፡፡ የ1996ቱ የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ እንዲወጣ ምክንያት ከነበሩት ወንጀሎችስ መካከል ዋነኞቹ የሙስና ወንጀሎች እንደነበሩ በወንጀል ሕጉ ዉስጥ ተጠቅሶ እናገኛለን፡፡ ከ1996 የኢ.ፌ.ዲ.ሪ. የወንጀል ሕግ ዉስጥ በተግባር የታዩ ችግሮችን በመፍታት የተሟላ የህግ ማዕቀፍ እንዲኖር በማድረግ የፀረ-ሙስና ትግሉን ለማጠናከር እና ሀገራችን ያለባትን አህጉራዊ እና ዓለም አቀፋዊ ግዴታ በአግባቡ እንድትወጣ ለማድረግ እና በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝባዉ ድርጅት ሰራተኞች፣በመንግስት የልማት ድርጅት ሰራተኞች እና በመንግስት ሰራተኞች የሚፈፀሙ ወንጀሎችን በማካተት ይዞ የወጣዉ የሙስና ወንጀሎች አዋጅ ቁጥር 881/2007 ነዉ፡፡

## 1.6 የሙስና ዓይነቶች

የሙስና መገለጫው ብዙ አይነት ሲሆን ከትናንሽ ጥቅማ ጥቅሞች አንስቶ እስከ ከፍተኛ ገንዘብ ዝርፊያና ምዝበራ እንዲሁም ከፍተኛ ጉዳት ሊያደርስ የሚችል ስልጣን አላግባብ መገልገል ሊሆን ይችላሉ፡፡ ከዚህ አንጻር ሙስና ዝቅተኛ (petty corruption)፣ ከፍተኛ (grand corruption) እና ሲስተሚክ (state capture) ሙስና ተብሎ ይከፈላል፡፡

### 1.6.1 ዝቅተኛ ሙስና (petty corruption)

ዝቅተኛ ሙስና ከከፍተኛ ሙስና አንጻር ሲታይ በመጠኑ አነስተኛ የሆነ የህዝብና የመንግስት ገንዘብ በሙስና ዝውውር ውስጥ የሚውልበት ነው፡፡ ዝቅተኛ የሙስና ወንጀል የሚፈጸመው

ከመንግስትና ከህዝብ አገልግሎት አሰጣጥና አቅርቦት ጋር በተያያዘ ሲሆን በዚህ የሙስና ወንጀል ውስጥ ተሳታፊ የሚሆኑት በቢሮክራሲው መዋቅር ውስጥ በየደረጃው አንዳንድ የመንግስት ሠራተኞችና ባለስልጣናት እንዲሁም ህገወጥ አገልግሎት ፈላጊ ግለሰቦች ናቸው፡፡

ዝቅተኛ ሙስና በመካከለኛና ዝቅተኛ የመንግስትና የህዝብ ተቋማት መጠኑ አነስተኛ የሆነ ገንዘብ አላግባብ የሚገኝበት ነው፡፡ መገለጫውም መለስተኛ እና ዝቅተኛ ደረጃ ላላቸው አገልግሎት አቅራቢዎች እንዲሁም ተገልጋዮች ከሚሰጥ አገልግሎት አቅርቦት (ፍቃድ መስጠት፣ ፍቃድ ማደስ፣ የትምህርትና የህክምና ማስረጃ መስጠት፣ አነስተኛ የኮንትሮባንድ እቃዎች ሳይቀረጥ ማሳለፍ የመሳሰሉት) ጋር የተያያዘ ነው፡፡ መጠኑ አነስተኛ የሆነ በአደራ የተቀበለውን ገንዘብና ንብረት መመዝበርን፣ ሰነዶችን በመሰረዝ እና በማጥፋት የማይገባ ጥቅም ማግኘትን፣ በግገር፣ በተሽከርካሪ ጥገና ስም የማይገባ ጥቅም መውሰድን፣ አብዛኛው ህዝብ አገልግሎት ለመጠየቅ ሲሄድ የሚያጋጥመው በመሆኑ ቶሎ የሚታወቅ ህዝቡን የሚያማርር፣ በህዝቡም ትኩረት የሚያገኝ ነው፡፡

### 1.6.2 ከፍተኛ ሙስና (Grand corruption)

ከፍተኛ ሙስና በአፈጻጸሙ በአጭር ጊዜ በረቀቀና ሚስጢራዊ በሆነ ስሌት በሚሊዮን የሚቆጠር የሀገር ሀብት የሚመዘበርበት፣ ስርቆትና ማጭበርበር የሚፈጸምበት ሲሆን ከፍተኛ የፖለቲካ እና የመንግስት ባለስልጣናትና ትልልቅ ባለሀብቶች የሚሳተፉበት የሙስና አይነት ነው፡፡ ከዚህ አኳያ የተሸሻለው የፌደራል የሥ-ነምግባርና የጸረ-ሙስና ኮሚሽን ማቋቋሚያ አዋጅ 433/1997 " ከባድ የሙስና ወንጀል" ማለት፤-

ሀ. ከፍተኛ ስትራቴጂያዊ ጠቀሜታ ባላቸው የመንግስት መስሪያ ቤቶችና የመንግስት የልማት ድርጅቶች ላይ የሚፈጸሙ ከፍተኛ የገንዘብ መጠንን ያካተቱ የሙስና ወንጀል ወይም

ለ. የመንግስት ባለስልጣንን የሚመለከቱ የሙስና ወንጀሎች ወይም

ሐ. በአገር ሉአላዊነት፤ኢኮኖሚ ፤ ጸጥታ እንዲሁም በህብረተሰብ ኑሮ ላይ ከፍተኛ ጉዳት የሚያደርሱ ወይም ሊያደርሱ ወይም የሚችሉ የሙስናንጀሎች ናቸው በሚል ይደነግጋል፡፡

### 1.6.3 ስርዓታዊ ሙስና (systemic capture)

የሀገሪቱን አጠቃላይ የመንግስት ስርዓት መዳከምና የተደራጁ የሙስና ወንጀል ፈጻሚ ሀይሎች የመንግስትን መዋቅር ከሞላ ጎደል ተቆጣጥረው የሚገኙበትን ሁኔታ የሚያመለክት ነው፡፡ የግልጽነትና ተጠያቂነት አሰራር ከሞላ ጎደል የላላ መሆን፣ ዋና ግባቸው የዝርፊያና ምዝበራ ስራ በሆኑ የተለያዩ ከፍተኛ የፖለቲካ ቡድኖች መካከል በሚፈጠር የጥቅም ግጭት የመንግስት መዋቅሩን አንድ ሆነው ለማጥቃት የሚጠቀምበት ሁኔታ መኖሩ ነው፡፡ ሲስተሚክ ሙስና ህግ አውጪውን፣ ምርጫ አስፈጻሚውን እንዲሁም የመንግስት አስፈጻሚ መዋቅሩን የአንድ ወይም የተደራጁ የፖለቲካ ቡድኖች የዝርፊያ እና ምዝበራ ፍላጎት መጠቀሚያ በማድረግ ይገለጻል፡፡ ከፍተኛ ሙስና ስር ሲሰድ ስርአታዊ (systemic capture ) በመሆን መንግስትን ሊቆጣጠር (state capture) ሊሆን የሚችል ነው፡፡

### 1.6.4 ፖለቲካዊ ሙስና (political Corruption)

በፖለቲካ ፓርቲዎች፣ በማንኛውም ደረጃ የፖለቲካ ውሳኔ በሚሰጡ ከፍተኛ የፖለቲካ አመራር አካላትና በመንግስት ባለስልጣናት በውሳኔ አሰጣጥ ላይ የሚፈጸም የሙስና ወንጀል ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና ብዙ ጊዜ ፖለቲካዊ ውሳኔዎች ለግልና ለቡድን ጥቅም በሚያመች መንገድ መወሰንን ወይም እንዲወሰኑ ማድረግንና የአንድን ማህበረሰብ ዴሞክራሲያዊ ሥርዓት፣ እሴቶችንና ልማዶችን የመጣስ ማንኛውንም ተግባር የሚመለከት ነው፡፡ ፖለቲካዊ ሙስና በተለያዩ መልኮች የሚገለጽ ቢሆንም ጎልተው የሚታዩ ዋና ዋናዎቹ የፖለቲካዊ ሙስና ዓይነቶች በምርጫ ወቅት የሚፈጸም ሙስና (Electoral Corruption)፣ የመንግስት ቢሮክራሲንና የመንግስት ሥራን ለፖለቲካ ጥቅም ማዋል (Politicization of bureaucracy) እንዲሁም በህግ አወጣጥ ሂደት ላይ የሚፈጸም ሙስና (Corruption in the legislative process) ናቸው፡፡ በአጠቃላይ በየተቋሙ የሚፈጸሙ የሙስና አይነቶች እንደየተቋማቱ አገልግሎት አሰጣጥ እና ተልዕኮ የሚለያዩ ናቸው ፡፡

## 1.7 የሙስና ወንጀል ልዩ ባህርያት

የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች የተለየና ዉስብስብ የሆነ ወንጀል ነው፡፡ የዚህን ወንጀል ከሌሎች የተለመዱ ወይም ነባር ወንጀሎች የተለየ የሚያድርጉትን ልዩ ሁኔታዎች ማወቅ የሙስና ወንጀልን ለመመርመር ፣ ለማጋለጥ ለመክሰስና አጥፊዎችን ለመቅጣት አስቸጋሪ

እንዲሆን የሚያድርጉትን ሁኔታዎች ለመረዳትና የተለየ ስልት ለመቀየስ ይረዳሉ። የሙስና ወንጀል ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች ልዩ ከሚያደርጉት መካከል የሚከተሉት ሊጠቀሱ ይችላሉ።

### 1.7.1 የወንጀሉ የአፈጻፀም ስልት

የሙስና ወንጀል በስሜት አልያም በጥላቻ ሳይሆን በሚስጢር፣ በስምምነት፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም ጥቅም ለማግኘት የሚፈጸም ነዉ። በዚህም ምክንያትም መፈፀሙን ለማወቅ የሚያችል ምንም አይነት ምልክት ማግኘት አዳጋች ነዉ። የሙስና ወንጀሎች በአብዛኛዉ የሚፈጸሙት በዘርፉ እዉቀት ባላቸዉ ባለሙያዎች ነዉ። ከዚህ በተጨማሪም በሚስጥር፣ በጥንቃቄ፣ እንዲሁም በቴክኖሎጂ በመታገዝ መፈፀሙ ብቻ ሳይሆን አጥፊዉ ለምርመራ መነሻ ሊሆን የሚችል ማስረጃ የማጥፋት አቅም ስላዉ ከነባር ወንጀሎች ለየት ያደርገዋል።

### 1.7.2 የሙስና ወንጀል የሚስከትለዉ ጉዳት

የሙስና ወንጀል የማይገባ ጥቅምን በማስገኘትና በማካበት፣ የማይገባ መብትን በመስጠት፣ ሌሎችን የሚገባቸዉን ሀብት በማጉደል ወይም መብታቸዉ ላይ በደል በማድረስ በዋናነት ፍትሀዊነት መንደልን ያስከትላል ። ለአንዱ ያለግባብ ፈቃድ ወይም መብት በመስጠት ሌሎችን በመንፈግ በዜጎች እና በሰዎች መካከል ሊኖር የሚገባዉን እኩልነት ያጠፋል። ከዚህ ባለፈም በአንድ ሀገር ሊኖር የሚገባ ማህበራዊ ፍትህ ወይም ፍትሀዊ የሀብት ክፍፍልን ያጠፋል። ዜጎችና እና ልማት የሚገባቸዉ የህብረተሰብ ክፍሎች የሚገባቸዉ መሠረታዊ አገልግሎት በጊዜና በጥራት እንዳይደረሳቸዉ ያደርጋል። በአጠቃላይ የሙስና ወንጀል ማህበራዊ፣ ኢኮኖሚያዊና ፖለቲካዊ ዘርፈ ብዙ ችግሮችን ያደርሳል።

### 1.7.3 የወንጀል ፈጻሚዎች አቅም

የሙስና ወንጀልን የሚፈጽሙት የመንግስት ሰራተኞችና ባለስልጣኖች የተሰጣቸውን ስልጣን መከታ አድርገው ሲሆን እነዚህ የመንግስት ሰራተኞች ግዴታቸውን እንዲጥሱ ለመንግስት ባለስልጣን በማማለያነት ጥቅም በመስጠትና አፍ በማዘጋት በወንጀሉ ተሳታፊ የሚሆኑ አላግባብ የመበልጸግ ፍላጎት ያላቸው ባለሀብቶች ለዚህ አላማ የሚያውሉት ሀብት ወይም ገንዘብ መኖሩ ነው። እነዚህ የመንግስት ባለስልጣንና አላግባብ በዘርፊያ መበልጸግ የሚፈልጉ ባለሀብቶች በእጃቸው ያለው ስልጣንና ገንዘብ የሙስና ወንጀሉ እንዳይመረመርና እንዲደበቅ ለማድረግ አቅም

የሚሰጣቸው ነው፡፡ ወንጀሉን ለማጋለጥ የሚፈልጉትን በማባበል እንቢ ካሉም በማስፈራራትና የበቀል እርምጃ በመውሰድ ጉዳዩ እንዳይጋለጥ ለማድረግና ተድበስብሶ እንዲቀር ለማድረግ የሚያስችል አቅም አላቸው፡፡ በእንዲህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የሙስና ወንጀልን ማጋለጥ፣ መመርመርና አጥፊዎችን ለህግ አቅርቦ ማስቀጣት ከባድ ነው፡፡

### 1.7.4 በወንጀሉ ቀጥተኛ ተጎጂ ግለሰብ አለመኖር

የተለመዱ ወይም ነባር በሚባሉት ወንጀሎች አጥቂና ተጠቂ ይኖራል፡፡ ከወንጀሉ ሁለቱም ተጠቃሚ ስለማይሆኑ አጥቂ የፈጸመዉን የወንጀል ድርጊት ተጠቂ የደረሰበትን በደል ለመካስ ስለሚያጋልጠዉ ወንጀሉን ለመመርመርና አጥፊዉን ለማስቀጣት ብዙም ችግር ላይገጥም ይችላል፡፡ በሙስና ወንጀል ግን ሁለቱም ተዋንያን ከወንጀሉ ተጠቃሚ ሊሆኑ ወይም በመንጀል ድርጊቱ ሊረኩ ይችላሉ፡፡ በወንጀሉ የተጠቀመ ወይም የረካ ሰዉ ደግሞ መደበቁን ይገፋበታል እንጂ ሊያጋልጥ አይችልም፡፡ ስለሆነም በዚህ ምክያት የሙስና ወንጀል ከመደበኛ ወይም ነባር ከሚባሉት የወንጀል አይነቶች በእጅጉ ይለያል፡፡

"የሁሉም የሆነ የማንም አይደለም" የሚል አባባል አለ፡፡ የሙስና ወንጀል በቀጥታ በአንድ ግለሰብ ወይም ቡድን ላይ የሚደርሰዉ ጉዳት ላይኖር ይችላል፡፡ በአንጻሩ በአገርና በዝዝብ ላይ የሚያደርሰዉ ጉዳት ግን እጅግ ከፍተኛ ነዉ፡፡ በዚህ ምክንያት ግለሰብ ወይም ቡድን በቀጥታ ተጠቂ ስለማይሆን ወንጀሉ ተፈጽሞ እንኳ ቢገኝ ያገባኛል ወይም የኔ ጉዳይ ነዉ ብሎ ጉዳዩን ለህግ የሚጠቁም እና አስፈላጊዉን ማስረጃ በማቅረብ እንዲመረመርና አጥፊዎች እንዲቀጡ የሚያደርግ ሰዉ ላይገኝ ይችላል፡፡ በዚህም ምክንያት ወንጀሉ ሳይጣራ ተዳፍኖ የሚቀርበት አጋጣሚ እጅጉ ብዙ ነዉ፡፡

### 1.7.5 ድንበር ተሻጋሪነቱ

ሰዎች የሙስና ወንጀለ የሚፈጽሙበት ዋነኛ ምክንያት ተገቢ ባልሆነ መንገድ ሀብትና ንብረት ለማፍራት ነዉ፡፡ በህገወጥ መንገድ የሚገኝ ሀብትና ንብረት ደግሞ ከፍተኛ በሚሆንበት ጊዜ ከአገር አልፎ ወደሌሎች አገሮች የመጓዝ አቅም ከመፍጠሩም በላይ እንደሽብርተኝነት ለመሳሰሉ ሌሎች ድንበር ተሻጋሪ ወንጀሎች መፈጠር አጋዥ በመሆኑን ሊጊሊግል ይችላል፡፡ ይህ ወንጀል ድንበር ተሻጋሪ በሚሆንበት ጊዜ ወንጀሉ ከአለም አቀፍ ድርጅቶች ወይም ግለሰቦች ጋር ትስስር

በመፍጠር ህጋዊ ሽፋን ተላብሶ ሊፈጸም ስለሚችል የወንጀል አፈጻጸሙን ስልት ዉስብስብ ያደርገዋል፡፡

## 1.8 በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉ የሙስና ወንጀሎች

የሙስና ወንጀል ድንጋጌዎች በአዋጅ ቁጥር 881/2007 ላይ ከአንቀጽ 9 እስከ 33 ላይ ተመልክቷል፡፡ በህጉ አወቃቀር መሠረት የሙስና ወንጀል ተብለው የተለዩት በ25 አንቀፆች የተጠቃለሉ ጉዳዮች ብቻ ናቸው፡፡

### 1.8.1 በሥልጣን ያለአግባብ መገልገል (አንቀፅ 9)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰው ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ፤ የተሰጠውን ሹመት፣ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት በግልፅ ተግባር(በማድረግ) ወይም በግድፈት(ባለማድረግ) ያለአግባብ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በግልፅ ከተሰጠው ሥልጣን ወይም ኃላፊነት አሳልፎ የሠራ እንደሆነ፤ ወይም ሥልጣን ወይም ኃላፊነት ሳይኖረው ወይም ከሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ ወይም ሥልጣኑን ወይም ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ የሠራበት እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.8.2 ጉቦ መቀበል (አንቀፅ 10)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን ለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ በቀጥታም ወይም በተዘዋዋሪ ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ጥቅም እንዲሰጥ ጠየቀ ፣የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.3 የማይገባ ጥቅም መቀበል (አንቀፅ 11)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በተሰጠው ኃላፊነት መሠረት ማድረግ የሚገባውን ተግባር ለማከናወን ሲል ይህንኑ ተግባር ከመፈፀሙ በፊት ወይም ከፈፀመ በኋላ

ጥቅም እንዲሰጠው የጠየቀ፣ ያገኘ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.4 አስታራቂ ሽማግሌዎችና ሌሎች ሰዎች የሚፈፅሙት ጉቦ የመቀበል ወንጀል (አንቀጽ 12)

ማንኛዉም አስታራቂ ሽማግሌ ፣የግልግል ዳኛ፣ የፍርድ ቤት ነባሪ ፣ ንብረት ጠባቂ ፣ወይም አጣሪ ፣ሥራዉን ለማካሄድ በባለስልጣን የተሾመ ተርጓሚ ወይም አስተርጓሚ ወይም በዳኝነት ወይም በዳኝነት ነክ በሚታይ ጉዳይ ላይ በሙያዉ ረገድ አስተያየቱን ወይም የምስክርነት ቃሉን

የሚሰጥ ማንኛዉም ልዩ አዋቂ (ኤክስፐርት) ፣ወይም ገቢና ወጪን ኦዲት የሚያደርግ ኦዲተር፣ ወይም ግንባታ በተገባዉ ዉል መሰረት መከናወኑን የሚረጋግጥ መሃንዲስ ማድረግ የሚገባዉን ላለማድረግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን ለማድረግ ጉዳ ከሚመለከተዉ ሰዉ ላይ ጥቅም እንዲሰጠዉ የጠየቀ ወይም ተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.5 የመንግስት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ስራን በማያመች አኳኋን መምራት (አንቀጽ 13)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለማግኘት፣ ወይም ለማስገኘት በማሰብ ሥልጣኑን ወይም ሃላፊነቱን ተጠቅሞ፦

በንግድ ወይም በሌላ ሥራ፣ በግዢ ወይም በሽያጭ ወይም ከሚያከናውነው ሥራ ጋር በተያያዘ በማናቸውም የሥራ ግንኙነት ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም የወሰደ ወይም ይህን ጥቅም የሚያገኝበትን ውል የተዋዋለ፤ ወይም ሌላ ዘዴ የፈጠረ እንደሆነ፤

አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ከተወሰነው በላይ በሆነ ዋጋ የዕቃ ማቅረብ ውል፣የሥራ መቋረጥ ውል ወይም ማናቸውም የሥራ ውል የተዋዋለ ወይም በዉል ከተመለከተው ዕቃ ወይም አገልግሎት ውጭ የተቀበለ እንደሆነ፤

በጠቅላላዉ በሥራዉ ሥልጣን ወይም ኃላፊነት መሠረት በአደራ የተሰጠዉን ወይም ሊጠብቀዉና ሊከላከለዉ የሚገባዉን የመንግስት መስሪያ ቤት፣ የመንግስት የልማት ድርጅት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ጥቅም የሚጎዳ ተግባር በማናቸዉም ዘዴ የፈፀመ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡

### 1.8.6 አደራ በተሠጠው ዕቃ ያለአግባብ ማዘዝ (አንቀፅ 14)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ በሕግ አግባብ ሳይፈቀድለትና የግል ንብረት ለማድረግ በማሰብ ሳይሆን ታሽጎ የተረከበዉን ጥቅል፣ ኢንቨሎፕ፣ ሰነድ፣ ባለዋጋ ነገር፣ ወይም እንደታሸገ የተረከበውን ማናቸውንም ዕቃ የከፈተ፣ ያስከፈተ፣ የወሰደ ወይም ያስወሰደ ወይም የእሽጉን ይዘት የገለጠ ወይም ዕቃውን አሳልፎ የሰጠ እንደሆነ፤ ወይም የተገለገለበት ወይም ሌላ ሰው እንዲገለገልበት የፈቀደ እንደሆነ ተጠያቂ ይሆናል፡፡

### 1.8.7 በሥራ ተግባር የሚፈፀም የመውሰድና የመሰወር ወንጀል (አንቀፅ 15)

የማይገባ ቁሳዊ ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ ማንኛዉም የመንግሥት ሠራተኛ በብርበራ፣ በመያዝ፣ በመውረስ ሥርዓት፣ በሐራጅ ሽያጭ፣ በህግ ውርስ ወይም ፍርዱ በንብረቱ ላይ እንዲፈፀም በመወሰኑ ወይም ይህን የመሰለ ማናቸውም ሥራ በሚያከናውንበት ወይም በሚያስፈፅምበት ጊዜ፤ ወይም የመንግሥት ወይም የሕዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በማንኛውም የሥራ አጋጣሚ በእጁ ሊገቡ የቻሉትን ወይም በአደራ የተረከባቸውን ወይም የሚጠብቃቸውን፤ ዕቃዎችን፣ ሰነዶችን፣ ባለዋጋ ነገሮችን፣ጥሬ ገንዘቦችን፣ ተንሳቃሽ ወይም አላቂ ዕቃዎችን የወሰደ ወይም የሰወረ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.8 በሥልጣን ወይም በኃላፊነት መነገድ (አንቀፅ 16)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በሥራው ምክንያት ባለው ወይም አስመስሎ ባቀረበው ተሰሚነት አግባብ ባለው ባለስልጣን ወይም ኃላፊ ተወስኖ የሚሰጥ የሥራ ደረጃ፣ ሹመት፣ ሥራ ፣ ሽልማት፣ የአገልግሎት ዋጋ፣ ልዩ ችሮታ፤ በቁጥጥሩ ወይም በአመራሩ ሥር በሚገኙ ባለስልጣኖች፣ኃላፊዎች ወይም የአስተዳደር ክፍሎች የሚደረግ ዉል፣የንግድ ስምምነት፣የስራ ጨረታ፣የዕቃ ማቅረብ ዉል ፣ወይም ሌላ ጥቅም ወይም በአጠቃላይ ከአንድ ባለስልጣን ፣ኃላፊ ወይም የአስተዳደር ክፍል የሚሰጠዉን ጥቅም ወይም የሚረዳ ዉሳኔ፣ ለሌላ

ሰዉ ለማስገኘት ስጦታ ወይም ሌላ ጥቅም የጠየቀ ወይም የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.8.9 በህገወጥ መንገድ መሰብሰብ ወይም ማስረከብ (አንቀፅ 17)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የማይገባ ጥቅም ለራሱ ለማግኘት በማሰብ ሊከፈል የማይገባ መሆኑን ወይም በህግ ከተወሰነው ታሪፍ በላይ መሆኑን እያወቀ ቀረጥ፣ ግብር፣ ልዩ ልዩ ገቢ ወይም ልዩ ልዩ የገቢ ጥቅም ፣ ምንዳ፣ ደመወዝ፣ ካሳ ወይም ሌላ ወጪ የሰበሰበ ወይም እንዲሰበሰብ ያዘዘ እንደሆነ፤ ማናቸውንም ዕቃ ወይም ክፍያ በሚያስረከብበት ወይም በሚሰጥበት ጊዜ ማስረከብ ወይም መክፈል ከሚገባው አሳንሶ ያስረከበ ወይም የከፈለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

### 1.1.10 ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት (አንቀፅ 18)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በሥራዉ ምክንያት በቀረበለት ጉዳይ ላይ ጥቅም ካለዉ ማንኛዉም ሰዉ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ ጥቅም ለማግኘት ፣በጉዳዩ ላይ ጥቅም ያለዉን ማንኛዉንም ወገን ለመጥቀም ወይም ለመጉዳት ሲል ከህግ፣ ከሥራ ደንብ፣ ወይም ከመመሪያ ወይም ከተለመደዉ አሠራር ዉጭ ያለ በቂ ምክንያት ያልወሰነ ፣ያዘገየ ወይም ባለጉዳዩን ጉላላ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.11 ዋጋ ያለውን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማግኘት (አንቀፅ 19)

ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረው ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸውንም ዋጋ ያለውን ነገር የተቀበለ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

ሁለተኛዉ በዚህ አንቀፅ የሚያስቀጣዉ ድርጊት ንብረትን፣ የፋይናንስ አቋምን፣ ስጦታ መቀበልን ማስመዝገብ ወይም ማሳወቅ እንደሚገባ በህግ ወይም በደንብ በተደነገገ ጊዜ አለማሳወቅ በተመሳሳይ ያስቀጣል፡፡ በአገሩ ወይም በአካባቢው ባህል ወይም ልማድ መሠረት እንደተራ

የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለው ሥጦታ መቀበል ወይም ከስጋ ወይም ከጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም የቅርብ ወዳጅ ስጦታ ማግኘት አያስጠይቅም፡፡

### 1.1.12 ያለአግባብ ፍቃድ መስጠት ወይም ማፅደቅ (አንቀፅ 20)

ማንኛውም የመንግሥት ሠራተኛ ሆነ ብሎ ወይም በቸልተኝነት፣ብቁ ላልሆነ ወይም በህግ ሊሰጠው ለማይገባ ሰው ማናቸውንም የንግድ ወይም የሥራ ፈቃድ የሰጠ ወይም ያፀደቀ ወይም እንደሆነ፣ ወይም አንድ ነገር የሚከናወንበትን ቦታ ያለአግባብ የፈቀደ ወይም የሰጠ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.13 ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ (አንቀፅ 21)

ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ የሆነ ወይም የነበረ ሰዉ የኑሮ ደረጃዉ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚያገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ የበለጠ እንደሆነ፤ ያለዉ ንብረት ወይም የገንዘብ ምንጭ አሁን ባለበት ወይም አስቀድሞ በነበረበት የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራ ወይም በሌላ መንገድ ከሚየገኘዉ ወይም ሲያገኘዉ ከነበረዉ ህጋዊ ገቢ ጋር የማይመጣጠን እንደሆነ በሙስና መንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.14 የሥራ ሚስጥርን መግለፅ (አንቀፅ 22)

አግባብነት ባለዉ ህግ አያስጠይቅም ተብሎ የተደነገገዉ እንደተጠበቀ ሆኖ ማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ለማግኘት ፣ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት ወይም በሌላ ሰዉ ጥቅም ወይም መብት ላይ ጉዳት እንዲደርስ ለማድረግ በማሰብ በሥራዉ ምክንያት ያወቀዉ ሆኖ በጠባዩ ሚስጥር የሆነዉን ወይም በሚስጥር እንዲጠበቅ የታዘዘዉን ወይም ለህዝብ እንዳይገለጽ የተከለከለዉን መረጃ ፣ሰነድ ወይም ፍሬ ነገር ሥራዉን ወይም ሹመቱን ከለቀቀ በኂላ ቢሆንም እንኳ የገለጸ ወይም የስተላለፈ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.15 መንግሥታዊ ወይም የህዝባዊ ሰነዶችን አስመስሎ ማዘጋጀት፣ ወደ ሐሰት መለወጥ

**ወይም በሐሰተኛ ሰነድ መገልገል (አንቀፅ 23)**

ማንኛዉም ሰው የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ተገቢ ያልሆነ ማናቸውንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት ታስቦ የሚፈፀም ነዉ፤ አንድ ፅሁፍ፣ መዝገብ ወይም ማንኛውንም ሰነድ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት በማስመሰል ያዘጋጀ ወይም የፈጠረ እንደሆነ፤

በመንግሥት ወይም በህዝባዊ ድርጅት መዝገብ ፣ፅሁፍ ወይም ሰነድ የሰፈረን እውነተኛ ፅሁፍ በመለወጥ ወይም በመደለዝ፣ በሐሰተኛ ፊርማ፣ በእጅ በተደረገ ምልክት ወይም በጣት ፊርማ፣ በማህተም ወይም የሌለውን ሥልጣን ወይም ችሎታ እንዳለው አስመስሎ በመፈረም ሐሰተኛ ሰነድ የፈጠረ፤ ወደ ሐሰት በተለወጠ ወይም በሐሰት በተዘጋጀ ሰነድ እያወቀ የተገለገለበት እንደሆነ፤ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

## 1.1.16 *መንግስታዊ ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰነዶችን ማጥፋት ወይም ጉዳት ማድረስ* (አንቀፅ 24)

ማንኛዉም ሰዉ የሌላዉን ሰዉ መብት ወይም ጥቅም ለመጉዳት ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰዉ ተገቢ ያልሆነ ማናቸዉንም መብት ወይም ጥቅም ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ በመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ወይም በህዝብ ሰነድ ላይ ጉዳት እንዲደርስበት ያደረገ ፣ የቀደደ፣ ያጠፋ ፣ጥቅም ላይ እንዳይዉል ያደረገ ወይም የወሰደ  እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠቃል፡፡

## 1.1.17 *ዋጋ ያለዉን ነገር ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ መስጠት* (አንቀፅ 26)

ማንኛዉም ሰዉ ተገቢ ምክንያት ሳይኖረዉ ለማንኛዉም የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ወይም ከእርሱ ጋር ግንኙነት ላለዉ ማንኛዉም ሌላ ሰዉ ያለክፍያ ወይም ያለበቂ ክፍያ ማናቸዉንም ዋጋ ያለዉ ነገር ያቀረበ ፣የሰጠ ወይም ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ያስጠይቃል ፡፡

በአገሩ ወይም በአካባቢዉ ባህል ወይም ልማድ መሰረት እንደተራ የወዳጅነት ምልክት የሚሰጥ ዋጋ ያለዉ ስጦታ መስጠት ወይም ለስጋ  ወይም ለጋብቻ የቅርብ ዘመድ ወይም ለቅርብ ወዳጅ ስጦታ መስጠት አያስጠቅም፡፡

### 1.1.18 ጉቦ ወይም ተገቢ ያልሆነ ጥቅም መስጠት (አንቀፅ 25)

ማንኛዉም ሰዉ አንድ የመንግስት ሠራተኛ ወይም የህዝባዉ ድርጅት ሠራተኛ በኃላፊነቱ ወይም በስራ ግዴታዉ ማድረግ የማይገባዉን እንዲያደርግ ወይም ማድረግ የሚገባዉን እንዳያደርግ ጥቅም ወይም ስጦታ የሰጠ ወይም ያቀረበ እንደሆነ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

### 1.1.19 ማቀባበል (አንቀፅ 27)

ማንኛዉም ሰዉ ለራሱ ማናቸዉንም ዓይነት ጥቅም ባያገኝም እንኳ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሥራን ለሚያከናዉን ሰዉ ጉቦ ለመስጠት ገንዘብ ፣ዋጋ ያለዉ ነገር ፣አገልግሎት ወይም ሌላ ዓይነት ጥቅም ከሌላ ሰዉ የተቀበለ እንደሆነ፤ ወይም የራሱን የባንክ ሂሳብ እንደዚህ ዓይነት ጉቦ ለማቀባበል ያዋለ እንደሆነ፤ ወይመ ጉቦ እንዲሰጣጡ ሁኔታዎችን ያመቻቸ ፣ያገናኘ ፣ ያስማማ ወይም የደለለ እንደደሆነ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡

### 1.1.20 በሌለው ሥልጣን መጠቀም (አንቀፅ 28)

ማንኛው‌ም ሰው ከመንግሥት ወይም ከህዝባዊ ድርጅት ሥራው ከታገደ፣ ከተዛወረ፣ ከተሻረ፣ ከተወገደ ወይም ሥልጣኑን፣ ኃላፊነቱን ከተወ በኋላ በሥራው ላይ ያለ በማስመሰል፤ለወደፊቱ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ እሆናለሁ ብሎ በማሳመን ወይም ሠራተኛ ሳይሆን መስሎ በመቅረብ፤ ይህንን አደርጋለሁ በማለት የተስፋ ቃል በመግባት ተገቢ ያልሆነ ጥቅም ወይም ሥጦታ ከሌላ ሰው የጠየቀ፣ የተቀበለ እንደሆነ ይጠየቃል፣

### 1.1.21 በግል ተሰሚነት መነገድ (አንቀፅ 29)

ማንኛውም ሰው የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ባይሆንም በሰዎች ዘንድ ያለውን ወይም እንዳለው ያስመሰለውን ተሰሚነት በመጠቀም በአንድ የመንግስት ወይም በህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ብቻ ሊሰጥ የሚችለውን ልዩ መብት ወይም ጥቅም እኔ አደርግልሀለሁ በማለት ለሌላ

ሰው ለማስገኘት ሲል ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የጠየቀ፣ የተቀበለ ወይም የተስፋ ቃል የተቀበለ እንደሆነ፤ በሙስና ይጠየቃል፡፡

ሰጭዉም ቢሆን የህግ ተጠያቂነት አገልግሎቱ የመንግስት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛ ብቻ እንደሚሰጥ እያወቀ ልዩ መብት ወይም ጥቅም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ለማስገኘት በማሰብ ገንዘብ፣ ስጦታ፣ ሌላ ጥቅም የሰጠ፣ ለመስጠት የተስማማ እንደሆነ ይጠየቃል፣

**1.1.22 በምርጫ ላይ የሚሰጥ መደለያ (አንቀጽ 30)**

*ማንኛውም ሰው የመምረጥ ወይም የመመረጥ መብት ያለው ሌላ ሰው በመብቱ በተወሰነ መንገድ እንዲጠቀም ወይም መብቱን እነዲተው ለማድረግ በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ገንዘብ ወይም በማናቸውም ሌላ አይነት ጥቅም የሰጠ፣ ወይም ለመስጠት ቃል የገባ እንደሆነ፣ በሙስና ወንጀል ይጠየቃል፡፡*

**1.1.23 ከባድ የእምነት ማጉደል (አንቀፅ 31)**

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለማስገኘት በማሰብ የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት የሆነውንና ለአንድ ለተወሰነ አገልግሎት ወይም በአደራ የተሰጠውን ዋጋ ያለውን ነገር፣ ጥሬ ገንዘብ በሙሉ ወይም በከፊል ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው ያደረገ፣ የወሰደ፣ ያስወሰደ፣ የሰወረ ወይም ለራሱ ወይም ለሌላ ሰው አገልግሎት ያዋለ፤መዉሰዱ፣ ማስወሰዱ ወዘተ በህግ ግምት የሚጣል በመሆኑ ዐቃቤ ህግ ንብረቱ መጉደሉን እንጂ መዉሰድ ማስወሰዱን ማስረዳት አይጠበቅበትም፡፡*

**1.1.24 ከባድ አታላይነት (አንቀፅ 32)**

*ማንኛውም የመንግሥት ወይም የህዝባዊ ድርጅት ሠራተኛ ተገቢ ያልሆነ ብልፅግና ለራሱ ለማግኘት ወይም ለሌላ ሰዉ ለማስገኘት በማሰብ አሳሳች የሆኑ ነገሮችን በመናገር፣ የራሱን ማንነት ወይም ሁኔታ በመሰወር ወይም መግለፅ የሚገባውን ነገር በመደበቅ ወይም የሌላውን ሰው የተሳሳተ እምነት ወይም ግምት በመጠቀም፣ በማድረግም ሆነ ባለማድረግ ሌላውን ሰው ማታለል በህግ የሚያስቀጣ ነዉ፡፡*

**1.1.25 በሙስና ወንጀል የተገኘን ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብና በወንጀሉ**

**ስለመርዳት (አንቀጽ 33)**

በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ህጋዊ አስመስሎ የማቅረብ ወንጀል የተፈጸመው በሙስና ወንጀል አመንጪነት ከሆነ አግባብነት ያለው በወንጀል ድርጊት የተገኘ ገንዘብ ወይም ንብረት ህጋዊ አስመስሎ ማቅረብ ህግ ተፈጻሚነት እንደተጠበቀ ሆኖ በሙስና ወንጀል ያስጠይቃል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አመቻቹ በሚያደራጁት ቡድን መሰረት ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. "ያለአግባብ ጉዳይን ማጓተት" በዘርፋችሁ እንዴት እንደሚስተዋሉ፤ የሚያስከትሉትን ጉዳት ተወያይታችሁ ለተሳታፊዎች አቅርቡ፤
2. በዘርፉ ተዘወትረው የሚታዩት የሙስና ወንጀል ዓይነቶች የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. "ምንጩ ያልታወቀ ንብረትና ገንዘብ ወንጀል" ን ለመከላከል የሃብት ምዝገባ እንዴት ሊከላከል እንደሚችል አስረዱ፡፡

## ማጠቃለያ

*በዚህ ምእራፍ ውስጥ ሙስና ለሚለው ጽንሰ ሃሳብ አንድ ወጥ የሆነ ዓለም አቀፋዊ ብያኔ መስጠት እንደማይቻል ተመልክተናል፡፡ በተጨማሪም የሙስና ወንጀል መገለጫ ጉቦ ብቻ እንዳልሆም መገንዘብ ተችሏል፡፡ ከዚህ አኳያ በአዋጅ ቁጥር 881/2007 የተደነገጉትን 25 የሙስና ወንጀሎችን ለማየት ተችሏል፡፡ በዚህ ምእራፍ ውስጥ የቀረቡት የሙስና ወንጀሎች ትርጓሜ ናቸው፡፡ የወንጀሎቹን ዝርዝር ጉዳይና የሚጣለውን መቀጮ በተመለከተ አዋጅ ቁጥር 881/2007ን ተጨማሪ ንባብ እንዲያደርጉ ይጠበቃል፡፡*

# ምዕራፍ ሁለት፦ የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት፣ስጋትና ብልሹ አሰራሮች

## 2.1 የምዕራፍ ሁለት መግቢያ

ለሙስና ተጋላጭነት ማለት በአንድ ተቋም ውስጥ የሚታዩ ሙስና ለመፈጸም የሚያመቹ የአሰራር ክፍተቶች እና ግድፈቶች መኖር ማለት ነው፡፡ ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ የአስተዳደር ዘርፍ የተለያዩ ተቋማት ለሙስና እና ብለሹ አሰራር ያላቸው ተጋላጭነት በዚህ ምዕራፍ ይዳሰሳሉ፡፡

## 2.2 የምዕራፍ ሁለት ዓላማዎች

**ሰልጣኞች ከዚህ ምዕራፍ ስልጠና በኋላ**

- የሙስና ተጋላጭነት ማለት ምን እንደሆነ ያስረዳሉ
- የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ለሙስና ተጋላጭ የሆኑባቸውን ምክንያቶቸ ይለያሉ፣
- በዘርፉ ዋና ዋና የሙስና ምንጮችን ይተነትናሉ፣
- ተጋላጭነትን በመለየት ሙስናን ለመከላከል ለተቋማቸውና ለማህበረሰቡ ሙስናን ለመከላከል የሚያግዙ ግንዛቤና ክህሎት የማስተማር/ የማሳወቅ ሚና ይወጣሉ፡፡

**የማሰልጠኛ ዘዴዎች፡-** የአእምሮን ጓዳ ማንኳኳት/Brain storming፣ገለፃ፣ጥያቄና መልስ፣ ውይይት፣አስረጅ ናሙና (case study)

**የሚወስደው ጊዜ፡-** 4፡00

**መርጃ መሳሪያዎች፡-** ፍሊፕ ቻርት፣ማርከር፣ፓወር ፖይንት፣ የተዘጋጀ ሰነድ

## 2.3 የሙስና ተጋላጭነት ምንነት እና ምክንያቶች

**የማነቃቂያ ጥያቄ፤**

ውድ ሰልጣኞች ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አጠገባችሁ ካሉ ተሳታፊዎች ጋር በቡድን በመወያየት ሃሳባችሁን ለተሳታፉዎች አቅርቡ፡፡

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች**

1. አንድ ተቋም በምን በምን ምክንያቶች ለሙስና ተጋላጭ ሊሆን ይችላል?
2. ለሙስና ተጋላጭነት ሆን ብሎ የሚፈጠር ነው ወይስ በአሰራር ሂደት የሚያጋጥም ነው?

## 2.4 በአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሙስና ተጋላጭነት እና ብልሹ አሰራሮች

ቀደም ሲል በዚህ ሞጁል መግቢያ እንደተገለጸው የአስተዳደር ዘርፍ ማለት በርካታ ተቋማትን በስሩ የያዘና ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ ወደ 18 የሚጠጉ ተቋማትን ይይዛል፡፡ የፌ/ሥ/ጸ/ሙ/ኮሚሽን በ2015 ዓም በቱሪዝም ዘርፍ ይህን የሙስና ሥጋት ችግር በዘላቂነት ለመቀነስ ሲባል በዘርፉ ስር ባሉ ተቋማት ውስጥ ለሙስና ሥጋት የሆኑ ጉዳዮችን ሙያዊና ስልታዊ የሆነ የተቋማት የስራ አፈፃፀም እና የሙስና ተጋላጭነት በ11 ርዕሰ-ጉዳዮች ላይ ግምገማዊ ጥናት በማካሄድ የሙስና የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል፡፡ ስለሆነም ለጠቅላይ ሚኒስቴር ጽ/ቤት ተጠሪ የሆኑ የተለያዩ ተቋማት ለሙስና ያላቸው ተጋላጭነት ምክንያቶች እንደሚከተለው ይቀርባሉ፤

### 2.4.1 የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አደረጃጀት

የስነ-ምግባር እና ጸረ ሙስና መከታተያ ቢሮዎች ሙስናን በመዋጋት ረገድ አይነተኛ ሚና እንደሚጫወቱ እሙን ነው፡፡ እያደገ እና እየተወሳሰበ የመጣውን ሙስና ወንጀል ለመከላከል፣ ተጠያቂነትን ለማስፈን ተቀማት መመስረታቸው አጅግ አስፈላጊ መሆኑ ይታመናል:: ከዚህ በላይ አጅግ ስፈላጊው ግን ተቋማቱ በሰው ሀይል እና በማቴሪያል የተደራጁ፣ጠንካራ እና ተነሳሽነታቸው ከፍ ያለ መሆን ይገባቸዋል፡፡

የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎች የቅንነት፣ ታማኝነት፣ ገለልተኝነት፣ ግልፅነት እና ተጠያቂነት ዋና እሴቶች ላይ የተመሰረተ ሥነምግባራዊ ድርጅታዊ ባህልን ለማጎልበት ከፍተኛ ሚና አላቸው:: በኢትዮጵያ እስካሁን ያሉት ግን በአብዛኛው በስም ብቻ ያሉ፤ደካማ የተብራራ ስራ ደርሻ የሌላቸው ናቸው:: በአብዛኛውም ተቋማት በጥርጣሬ የሚታዩ ናቸው፡፡ አንዳንድ ተቋማትም በጭራሽ መከታታያ ቢሮ የላቸውም፡፡ ለምሳሌ  የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ስራ አመራር እና የፕሬዝዳንት

ጽ/ቤት ለክፍሉ አንድ ባለሙያ ብቻ ሲመድቡ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ከተፈቀደው የስራ መደብ ውስጥ 100 በመቶ አላሟሉም (የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥናት (2015) ። በመሆኑም አይቸሀለሁ የሚል ተቋም አለመኖሩ ሙስናን በስፋት ለመፈጸም አመቺ ይሆናል ማለት ነው።

ከላይ እንደተጠቀሰው የስነምግባር እና ፀረ ሙስና መከታተያ ቢሮዎች ሙስናን በመውጋት አይነተኛ ሚና ይጫወታሉ፡ ነገር ግን የበርካታ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደቦች በሰው ኃይል ያልተሟሉ መሆናቸው የስነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ኮሚሽን ጥናት ግኝት አመላክቷል። ይህም ተገቢውን የሙስና ስጋት ግምገማ በማካሄድ አደጋን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከል ስልት ለመንደፍና የቁጥጥር ስርአትን ለማዳበር የሚያስችል አደረጃጀት እንደሌላቸው ጠቋሚ ነው።

የስነ-ምግባር እና ፀረ-ሙስና መከታተያ ቢሮዎች ሙስና እና ብልሹ አሰራሮችን አነፍንፎ እና መንጥሮ ለማውጣት አቅማቸው የጎለበተ፣በታታሪ ሰዎች የሚመሩ እና አስፈላጊው ድጋፍ የሚደረግላቸው ሊሆኑ ይጋባል። በጥቅማጥቅም የማይደለሉ እና በማስፈራራት የማይንብረከኩ ሊሆኑ ይገባችዋለ። ሀሉም ተቋማት መከታተያ ቢሮዎች እንዲናራቸ ማድረግ ያስፈልጋል።

የፌ/ሥ/ጸ/ሙ/ኮሚሽን በ2015 በአስተዳደር ዘርፍ ያስጠናው ጥናት መከታተያ ክፍሎችን በተመለከተ የሚከተሉተን አንካር ነጥቦች አስቀምጧል፤

- የበርካታ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍል የስራ መደቦች በሰው ኃይል አልተሟሉም። ይህም ተገቢውን የሙስና ስጋት ግምገማ በማካሄድ አደጋን መሰረት ያደረገ የሙስና መከላከል ስልት ለመንደፍና የቁጥጥር ስርአትን ለማዳበር የሚያስችል አደረጃጀት እንደሌላቸው ጠቋሚ ነው።
- በተለይ በሁለት ተቋማት ውስጥ የሥነምግባር መከታተያ ክፍል አለመደራጀቱ አመራሩ ሥነምግባርን በማስረፅ ረገድ የሚጠበቅበትን ኃላፊነት በቸልተኝነት ወደጎን እንደተወ አመላካች ነው።
- በዘርፉ ውስጥ የሚገኙ የተወሰኑ ተቋማት የሥነምግባር መከታተያ ክፍሎቻቸው ከሌሎች ክፍሎች ጋር በቅንጅት ስለመስራታቸው የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም።
- ከግማሽ በላይ በሚሆኑ የዘርፉ ተቋማት ውሎች ከመፈረማቸው በፊት በህግ ክፍል አስተያየት የሚሰጥበት አሰራር ወጥነት ባለው መልኩ ተግባራዊ አለመደረጉ የመንግስትን

ጥቅም ሊጎዱ የሚችሉ ውሎች በሙስና ድርድር/ስልጣንን አላግባብ በመጠቀም ተፈፃሚ ሊሆኑ የሚችሉበት ምቹ ሁኔታ ሊፈጥር ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው፡፡

**ኬዝ አንድ፤ የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች ከታች የተመለከተው ናሙና/ኬዝ ላይ የቡድን ውይይት አድርጋችሁ ውጤቱን አቅረቡ፡፡

ከላይ እንደተጠቀሰው የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ጥናት በ2015) ያስጠናው ጥናት እንዳመለከተው የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ፣ የኢትዮጵያ ኮሚዩኒኬሽን ባለስልጣን፣ የሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን፣ የኢትዮጵያ ስራ አመራር እና የፕሬዝዳንት ጽ/ቤት **ለስነ-ምግባር እና ጸረ-ሙስና መከታተያ** ክፍሉ አንድ ባለሙያ ብቻ ሲመድቡ፣ የኢትዮጵያ ብሔራዊ ባንክ እና የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት ከተፈቀደው የስራ መደብ ውስጥ 100% አላሚሉም፡ ለመከታተያ ክፍሉ ያልተሟላ የሰው ሀይል መኖሩ እንዲሁም ጭራሽ መከታተያ ክፍሉ አለመኖሩ ተቋማቱን እንደት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭ ያደርጋል?

### 2.4.2 ተጠያቂነትን ማስፈን

የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው፡፡ የዚህ ስርአት በአግባቡ ተግባር ላይ መዋል ማንኛውም አመራር/ሰራተኛ ከተሰጠው ስልጣንና ከተጣለበት ኃላፊነት አንፃር በአፈፃፀሙ፣ በውሳኔውና በሚያስከትላቸው ተፅዕኖዎች እንደሚገመገም እንዲሁም ብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ከተረጋገጠ አንደአስፈላጊነቱ የእርምት እርምጃዎች እንደሚወሰዱ ማረጋገጫ ይሰጣል፡፡

በየፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015) ጥናት ተጠያቂንትን ከማስፈን አጻር የሚከቱልቱነ ግኝቶች አእና የሚያስከትሉትን ጉዳት አእንድሚከተለው አስቀምጧል፤

- በጠቅላይ ሚኒስቴር ዘርፍ ስር ከሚገኙት ተቋማት መካከል ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱት ስድስቱ ብቻ ናቸው፡፡ ከዚህ ጋር በተያያዘ ጥናቱን ተመርኩዞ አሠራራቸውን የማሻሻልና የማረም ሥራ የሰሩት ሶስት ተቋማት ብቻ መሆናቸው ለሙስና የተጋላጭነት ስጋት መኖሩን ያመለክታል፡፡

- በዘርፉ ስር ካሉ ተቋማት መካከል የደንበኞች እርካታን በየጊዜው በገለልተኛ አካል ያስጠኑት ብሔራዊ ባንክ እና የመንግስት ሠራተኞች ማህበራዊ ዋስትና አስተዳደር ሲሆኑ፣ ሌሎቹ ተቋማት ይህን ማከናወናቸውን የሚገልፅ መረጃ አልቀረበም።
- የተሳሳቱ ድርጊቶች ከመፈፀማቸው በፊት ጥቆማ ደርሶ ቅድመ-መከላከል ሥራዎችን የሠሩት አምስት ተቋማት ብቻ ናቸው። በሌሎች 13ቱ ላይ የቅድመ መከላከል ሥራ ስለመሠራቱ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም።
- በዘርፉ ስር የሚገኙ አምስት ተቋማት የሥነምግባር ደንብ አለማዘጋጀታቸው ከጠያቂነት አንጥጻር ዋናዋና ስጋቶች ናቸው።

### 2.4.3 የተቋማት ግልፅነት

ተጠያቂነት ከሌለ ማንም ሰዉ ያሻዉንና የፈቀደዉን እንዲሰራ ምክንያት ይሆናል።አንድ ሰዉ ያሻዉን ሲሰራ የማይጠየቅ ወይም ቁጥጥር የማይደረግበት ከሆነ ደግሞ ሙስና ይከሰታል። የተጠያቂነት ስርአት የተቋማት ሀላፊዎች እና ሰራተኞች ለድርጊታቸው፣ ለባህሪያቸው፣ ለአፈፃፀማቸው እና ለሚወስዷቸው ውሳኔዎች ኃላፊነት የሚወስዱበት የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው። ከዚሀ አንጻር በዘርፉ በሚገኙ ተቋማት ውስጥ አሳሳቢ ጉዳዮች አሉ። ለምሳሌ በአስተዳደር ዘርፍ ስር ከሚገኙት 18 ተቋማት መካከል ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱት ስድስቱ ብቻ መሆናቸው እና ሌሎቹ አለማካሄዳቸው ትልቅ ክፍተት ነው።

በተጨማሪም ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ መገለጫ ነው። ይህን በተመለተ በሁሉም የዘርፉ ተቋማት ውስጥ እቅዶች እና የእቅድ አፈፃፀሞች በጋራ ውይይት የሚደረግባቸው መሆኑን ጥናቶች አመላክተዋል።ይህ ይበል የሚያስብል ታላቅ ተግባር ነው።ነገር ግን ገሚሱ የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ መረጃ አላቀረቡም። እንዲሁም የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም። ይህም ግልፅነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል።

የመንግስት ተቋማት የሚያከናውኗቸው ተግባራት ግልፅነትን ሊላበሱ ይገባል፡፡ ግልፅነት ዜጎች ለህብረተሰቡ አገልገሎት ለመስጠት የተዋቀሩ ተቋማትን የስራ አፈፃፀም እንዲሁም የሚከሰቱ ችግሮችን መንስኤ እና መዘዞችን በተመለከተ በቂ መረጃ እንዲያገኙ የሚያስችላቸው የመልካም አስተዳደር ወሳኝ ገጽታ ነው:: የመንግስት አካላት የውሳኔዎች፣ የፖሊሲዎች እና የውጤቶች አተገባበር መረጃ ለህብረተሰቡ ተደራሽ መሆናቸውን ማረጋገጥ ያጠቃለለ ነው፡፡ በኮሚሽኑ 2015 ጥናት የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል፡፡

- ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት በስራ ሂደቶች ውሳኔ አሰጣጥ ሂደት ላይ የሚመለከታቸው አካላት እንደሚሳተፉ መረጃ አለመቅረቡ እና የተለያዩ ውሳኔዎች እና ቃለጉባዔዎች ተደራሽ ስለመደረጋቸው የሚያሳይ መረጃ በአብዛኛው የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም፡፡
- የግዥና ጨረታ ማስታወቂያዎችን በተለያዩ ሚዲያዎች (ጋዜጣ፤ ሬድዮ፤ ቴሌቭዥን፣ ወዘተ) በይፋ ማሰራጨትን በተመለከተ 15ቱ የዘርፉ ተቋማት የሚያሰራጩ ሲሆን ቀሪዎቹ ሶስቱ አለማድርጃቸው አእንደስጋት ተወስዷል፡፡

### 2.4.4 አዋጅ፣ ደንብና መመሪያ

ሙስናን ለመዋጋት ከሚያስችሉ ጉዳዮች መካከል አዋጆች፣ ደንቦችና መመሪያዎች ሚናቸው ከፍተኛ ነው፡፡የህግ የበላይነት ከማስፈን ባሻገር ተግባራዊ መደረግ ያለባቸውን መርሆች በመደንገግ ፈፃሚዎች ስራቸውን ህግን በተከተለ መሰረት እንዲሰሩ አስገዳጅ ሁኔታን ይፈጥራል፡፡

ከዚህ አንጻር በኮሚሽኑ 2015 ጥናት የሚከተሉት ስጋቶች ተለይተዋል፡፡

- ከግማሽ በላይ በሚሆኑት የዘርፉ ተቋማት የዜጎች ቻርተር ስለመዘጋጀቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ ቻርተሩን ካዘጋጁትም ውስጥ የተወሰኑት በተገቢው መንገድ ለተገልጋዮች ተደራሽ አላደረጉም፡፡
- በተጨማሪም ገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ፀድቀው የሚወጡ መመሪያዎችን ለተገልጋዮች/ ለተጠቃሚዎች በቀላሉ ተደራሽ ማድረጋቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም
- ሲሶው የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ለአመራርና ሰራተኞች በአዋጅ፣ ደንብና መመሪያ አተገባበር ላይ ስልጠና ስለመሰጠቱ መረጃ አልቀረበም፡፡ ይህ ጉድለት በሠራተኞች የሥራ አፈፃፀም ላይ ከሚያሳድረው አሉታዊ ተፅዕኖ በተጨማሪ ሠራተኞች ከዕውቀት ክፍተት ጋር ተያይዞ ለብልሹ አሠራር እንዲጋለጡ ሊያደርግ ይችላል፡፡

### 2.4.5 የንብረት አስተዳደር

በየፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015) ጥናት መሰረት በዘርፉ ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ አብዛኛው ለጠቀላይ ሚ/ር ቢሮ ተጠሪ የሆኑ መስሪያ ቤቶች ንብረት አስተዳደር ያላቸው ቢሆንም በስርዓት መተደራጀት ላይ ግን ውስንነቶች አሉበት፡፡ ንብረት አስተዳደር በተለምዶ ንብረት ክፍል የሚባለው በርካታ ተግባራትን ያክናውናል፡፡ማንኛውም ተግዝቶ የሚመጣን እቃን ጥራት የማረጋገጥ ህላፊነት አለበት፡፡ እንዲሁም ያገልገሉ ንብረቶች እንዲወገዱ ያደርጋል፡፡ ንብረትን ከርክክብ እስክ ማስወገድ ድረስ ያለው ሃላፊንት የንብረት ክፍል ነው፡፡

የስነ ምግባር እና ፀረ ሙስና ኮሚሽን ያስጠናው ጥናት በዘርፉ ሥር በሚገኙ ሁሉም ተቋማት ንብረት የማስተዳደርና የመቆጣጠር አሠራር ሥርዓት መዘርጋቱን ያሳያል፡፡ በዘርፉ ሥር ባሉ 17 ተቋማት ዓመታዊ የንብረት ቆጠራ እንደሚደረግ ከተሰበሰቡ መረጃዎች መገንዘብ ተችሏል፡፡ በፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ግን ዓመታዊ ንብረት ቆጠራ ስለመደረጉ የሚያሳይ መረጃ አልቀረበም (የፌዴራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን (2015)፡፡ በመሆኑም በጣም ተጋላጭ ከሚባሉት ተቋማት አንዱ ነው ማለት ነው፡፡

በተጨማሪም የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት በዘመነ መልኩ ንብረት የሚመዘግቡበት እና አገልገሎት የማይሰጡ ንብረቶችን የሚያስግዱበት ቀልጣፋ ስርዓት የላቸውም፡፡ አንዳንዶቹ አዲስ እና አሮጌ እቃዎችን በአንድ ላይ ያስቀምጣሉ፡፡አገልግሎት የማይሰጡ ንብረቶችንም አገልግሎት መስጠት የሚችሉትንም ለረጅም ጊዜ በማስቀመጥ ለብልሽት እና ብክነት እንዲዳረጉ ያደርጋሉ፡፡

የንብረት አስተዳደር ለሙስና ተጋላጭ የሚሆንባቸው መንገዶች፤

1. ንብረቶች በሚገባ ሳይመረመሩ ሊወገዱ ይችላሉ
2. በመደራደር ከጥራት በታች የሆኑ ዕቃዎች ገቢ ሊሆኑ ይችላሉ
3. መስፈርቶችን አወዛጋቢ በማድረግ ጥቅም ሊያጋብሱ ይችላሉ።

ከንብረት አያያዝ አእና አወጋገድ ጋር የታዩ ክፍተቶች እና ስጋቶች፤

- በሶስት ተቋማት የሚወገዱ ንብረቶች ዝርዝራቸው ቀርቦ በሚመለከታቸው ባለሙያዎች ተገምግመው የሚወገዱ መሆናቸውን የሚያሳይ መረጃ አልተገኘም፡፡
- የካይዘን ንብረት አስተዳደር ስርዓትን የተገበሩት ከግማሽ በታች የዘርፉ ተቋማት ብቻ መሆናቸውን በምልከታ ለማረጋገጥ ተችሏል፡፡ ይህ ስርአት አለመተግበሩ እቃዎች በበቂ

መጠን በመጋዘን ባሉበት ሁኔታ ተጨማሪ ግዥዎችን በማከናወን የህዝብን ሃብት ለብልሽት እና ብክነት ሊያጋልጥ ይችላል፡፡

### 2.4.6 የግዥ አስተዳደር

የግዥ ክፍል የተቋማት ጥፋት ወይም ልማት መሰረት መሆኑ በሚገባ ይታወቃል፡፡ ጥናት እንደሚያለክተው ከ18ቱ ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ተጠሪ ተቀማት 13ቱ የግዥ እቀድ አፈጻጸም ግምገማ የሚያደርጉ ሲሆን ለሌቹ ደግሞ ይህን ስለማድረጋቸው መረጃ አልቀረበም፡፡ የግዥ አፈፃፀምን በተመለከተ 11 ተቋማት ግምገማ ያካሄዱ ሲሆን ቀሪዎቹ ሰባት ተቋማት ግን የግዥ አፈፃፀም ግምገማ ስለማድረጋቸው መረጃ ያላቀረቡ ናቸው፡፡ አንዳንዶቹ ካለ እቅድ ይገዛሉ፤በስቶክ መኖራቸውን ሳያረጋግጡ የሚገዙ አሉ፤ ድጅታላይዝድ የግዥ ስርዓት ይጎድላቸዋል፡፡

በዘርፉ ስር ከሚገኙ 18 ተቋማት ውስጥ 12ቱ ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት ንብረቶቹ በስቶክ መኖር ወይም አለመኖራቸው የሚረጋገጥበት ሥርዓት የዘረጉ ሲሆን፣ ሌሎቹ ደግሞ መረጃ አላቀረቡም፡፡ ግዥ ክፍል ለተቋማት የጀርባ አጥንት ስለሆነ ጤናው የተስተካለ ከሆነ የተቋሙ ጤንነት በአብዛኛው ይስተካከላል፡፡ እሱ ጤናው ከታወከ የተቋማቱ ጤና ይታወካል፡፡ በግዥ ከፍል ጋር በበርካታ መንገዶች ሙስና ሊከናወን ይችላል፡፡

**የግዥ ክፍል ለሙስና ተጋላጭ የሚሆንባቸው ምክንያቶች፤**

- ከፍተኛ ገንዘብ/በጀት ስለሚያንቀሳቅስ፣
- የግዥ ሂደት ውስብስብ ስልሆነ፣
- የግዥ አፈጻጸም ረጅም ሂደት የሚያልፍ በምሆኑ፣
- በርካታ ከባቢያዊ ገፊ ምክንያቶች ስላሉ፣
- በርካታ አካላት ስለሚሳተፉበት።

በአስተዳደር ዘርፍ ላይ የተደረገው ጥናት እንደሚያሳየው፤

- ወደ ሁለት-ሶስተኛ የሚጠጉ የዘርፉ ተቋማት ዲጂታላይዝድ የግዢ ስርአት እንዳልተገበሩ ታውቋል፡፡
- ሲሶው የዘርፉ ተቋማት ግዥ ከመፈጸማቸው በፊት ንብረቶቹ በስቶክ መኖር ወይም አለመኖራቸው የሚረጋገጥበትን ሥርዓት የዘረጉ ስለመሆኑ መረጃ አልቀረበም፡፡

- በገሚሱ የዘርፉ ተቋማት ውስጥ ግዥ ሲከናወን በገበያ ጥናት ላይ የተመሰረተ አለመሆኑ ለተጋነነ የምርቶች/አገልግሎቶች ዋጋ ስለሚጋብዝ የሙስና ስጋት ነው።
- የተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት የግዥ ዕቅድ እንዲሁም የግዥ ዕቅድ አፈፃፀም ላይ ግምገማ እንደሚያከናውኑ በማስረጃ ሊረጋገጥ አልቻለም። ይህም ግልፅነት እና ተጠያቂነትን ከማስፈን አኳያ በዘርፉ ውስጥ እጅግ አሳሳቢ የሆኑ ክፍተቶች እንዳሉ ያሳያል።
- በዘርፉ ተቋማት በርካታ ሚሊዮን ብሮች ግምት ያላቸው የፕሮፎርማ ግዢዎች፣ የውስን ጨረታ ግዢዎች፣ ከአንድ አቅራቢ ተደጋጋሚ ግዥዎች እና ያለዕቅድ ግዥዎች መከናወናቸው የግዥ ዕቅዶች ክፍተት እንዳለባቸው አመላካች ናቸው።

**ጽብረቃ/** Reflection

- በተቋማችሁ ውስጥ በሚከናወነው የግዥ ተግባር ላይ የሚከሰተው ሙስና አይነት ዋነኛ ምክንያት አድርጋችሁ የምታቀርቡት ምንድን ነው? ለቀረበው ምክንያት መከላከያ ይሆናል የምትሉትስ ምንድን ነው?

ሙስና የሚፈጸምበት መንገድ እየረቀቀ፣ተዋናዮቹ እየበረከቱ፣ መጠኑም እየጨመረ ከነውርነቱ ይልቅ የተለመደ የማያሸማቅቅ ተግባር እየሆነ ነው። በርካታ ሃላፊዎችም ***'መቼም ሰው ነህና ለገንዘብ ትሸነፋለህ የተባለ ይመስል"*** ለገንዘብ እየተንበረከኩ ይመስላል። በመሆኑም ጠበቅ ያለ ክትትል እና ርምጃ መውሰድ ያስፈልጋል።ተቋማት በተለይ የግዥ ክፍሎቻቸውን እንቅስቃሴ እና ሁኔታ፣የጥራት ተቆጣጣሪዎችን ብቃት እና ታማኝነት፣አንድ ተቋም ለምን ሁል ጊዜ የጨረታ አሸናፊ የሚሆንበት ሁኔታ ላይ ክትትል አለማድረግ ለሙስና ተጋላጭ ያድርጋቸዋል።

### 2.4.7 የሰው ሀብት አስተዳደር

የአንድን ተቋም ስኬት ከሚወስኑ መሰረታዊ ግብኣቶች ውስጥ በዋናነት የሚጠቀሰው ያላቸው የሰው ሃብት ነው። ስኬት የሚረጋገጠው የሰው ሃብት በአግባቡ ማስተዳደር ሲቻል ነው። ለዚህ የሚያግዙ አሰራሮችና መዋቅሮች መዘርጋት ተገቢነቱ የጎላ ነው። የብዙ ተቀማት የሰው ሀብት አስተዳር የሚመራው አቅም እና ስነ-ምግባር በሌላቸው ሰዎች ነው። የሰው ሀብት አስተዳዳር ሰዎች ብቃት ያለው ሰው ለመቅጠር እና ተቋማቸው ተጠቃሚ ለማድረግ ብዙም ግድ አይሰጣቸውም። ከዚህ አንጻር ከአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ላይ የተጠናው የጥናት ውጤት የሚከተሉትን ከሰው ሀብት አስተዳደር ጋር የተያያዙ ችግሮችን ለይቷል።

- ሀሰተኛ የትምህርትና የስራ ልምድ ሰነድ የማጣራት ስራ በ14ቱ የዘርፉ ተቋማት እንዳልተከናወነ በጥናቱ ተረጋግጧል፡፡
- በዘመናዊ ቴክኖሎጂ የታገዘ የሰው ሃብት አስተዳደር ስርአት በተወሰኑ የዘርፉ ተቋማት አለመገንባቱ በቅጥር፣ ዝውውር፣ እድገት፣ ወዘተ ውሳኔዎች ላይ አሉታዊ ተፅእኖ ሊያስከትል ይችላል፡፡
- በሥነምግባር ዙሪያ የስልጠናዎች አለመኖር አመራርና ሰራተኞች ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዲፀየፉና እንዲታገሉ ለማድረግ የሚደረገውን ጥረት በሚፈለገው ልክ ከግብ እንዳይደርስ ሊያደርግ የሚችል ክፍተት ተደርጎ ሊወሰድ ይችላል፡፡

| **የጥንድ ውይይት** |
| --- |
| ➢ ውድ ሰልጣኞች በሰው ሀብት አስተዳደር አካባቢ ሊፈጸሙ የሚችሉ የሙስና አይነቶችን ዘርዝሩ፡ |

## 2.4.8 የሃብት ምዝገባና ማሳወቅ

የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተፈራ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጥልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው፡፡የሃብት ምዝገባ ሙስናን አስቀድሞ ለመከላከል፣ ተቋማዊ ኃላፊነትና የግል ጥቅም ሳይጋጩ በራሳቸው መንገድ እንዲመሩ ለማድረግ፣ አላግባብ የተፈራ ምንጩ ያልታወቀ ሃብትን ለማጋለጥ እና መልካም አስተዳደርን ለማስፈን ጥልቅ ፋይዳ ያለው ሥርዓት ነው፡፡

ከዚህ አኳያ የኮሚሽኑ የ2015 ጥናት አእንዳሳየው በበዘርፉ ሥር የሚገኙ የሁሉም ተቋማት አመራሮች እና ሰራተኞች ሃብታቸውን በhardcopy እንዳስመዘገቡ መረጃዎች ያሳያሉ፡፡ ሆኖም በሲስተም ሙሉ ለሙሉ ያስመዘገቡ የፌዴራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን እና አርቴፍሻል ኢንተለጀንስ ኢንስቲትዩት ብቻ ናቸው፡፡ በሲስተም ማስመዝገብ እስካሁን ያልጀመሩ ደግሞ ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን እና የኢንፎርሜሽን መረብ ደህንነት አገልግሎት ናቸው፡፡ ቀሪዎቹ አፈፃፀማቸው በተለያየ ደረጃ ላይ ይገኛሉ፡፡

### 2.4.9 የፕሮጀክቶች አስተዳደር

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ክትትል የሚያደርግ አካል ከሌለ ለጥራት እና ጉድለት ይጋለጣሉ። የኮንስትራክሽን ፕሮጀክት ዘርፍ ሙስና ከፍተኛ ሁኔታ የሙስና ለም መሬት እንደሆን ይታመናል። እነኚህ ፕሮጀክቶች ግዙፍ የሆነ በጀት የሚያንቀሳቅሱ በመሆናቸው ነው። ስለሆነም ልዩ ክትትል እና ቁጥጥር ያስፈልገዋል። የኮንስትራክሽን ፕሮጀክትን በተያዘለት የጊዜ ሰሌዳ፣ በጀትና የጥራት ደረጃ ለማጠናቀቅ የዲዛይን ጥራት፣ የጨረታ አወጣጥ ሂደት፣ የክፍያ ስርአት፣ የኮንትራት አስተዳደር እና ከመሰል ጉዳዮች ጋር ተያይዞ የተጠናከረ የክትትልና ቁጥጥር ሥርዓት መዘርጋት ያስፈልጋል።

ፕሮጀክቶች ከቅድመ ግንባታ እስከ ፍፃሜቸው ድረስ አግባብነት ያላቸውን ህጎችና መስፈርቶች ተከትለው እየተፈጸሙ ስለመሆናቸው ቴክኒካል ቁጥጥርና ክትትል የሚያደርግ የተለየ የኦዲት መዋቅር ባለመኖሩ፣ በተለያዩ አካላት የሚገነቡ ፕሮጀክቶች ለጥራት መጓደልና ብክነት እየተጋለጡ መሆኑን ጥናቶች ያሳያሉ።

በዘርፉ ስር ከሚገኙ ተቋማት ውስጥ ተጀምረው በጊዜያቸው ያልተጠናቀቁ ፕሮጀክቶች መኖራችውን ጥናቱ ያሳያል። በተጨማሪም በድምሩ 13 ሚሊዬን ብር የሚሆን የዋጋ ማስተካከያ የተደረገባቸው ፕሮጀክቶች በአደጋ ስጋት ሥራ አመራር ኮሚሽን መኖራቸውን የተሰበሰቡ መረጃዎች ያሳያሉ። የገንዘብ መጠኑ በድምሩ 1.5 ቢሊዬን ብር የሚሆኑ ተጨማሪ ሥራ የተሰጠባቸው ፕሮጅከቶቸ ለጠቅላይ ሚ/ር ተጠሪ በሆኑ ተቋማት ውስጥ አሉ።

ጨረታ አውጥቶ ማወዳደር እየተቻለ ከአንድ አቅራቢ ያለጨረታ እንዲገዛ ማድረግ አቅራቢው ያለውድድር ከፍተኛ መጠን ያለው ግዢ በማድረግ ተጠቃሚ ይሆናል። ምንም እንኳን የተገዛበት ዋጋ በገበያ ዋጋ ቢሆንም፣ያለጨረታ ጥቅም እንዲያገኝ ማድረግ አግባብ ባልሆነ መንገድ የተገኘ ጥቅም ስለሆነ ድርጊቱ የሙስና ወንጀል ይሆናል ማለት ነው።

የፌደራል ሥነ-ምግባርና ፀረ ሙስና ኮሚሽን የ2015 ጥናት የሚከተሉትን ስጋቶች ያሳያል፤

- የፕሮጀክቶች በተያዘላቸው የጊዜ ገደብ ያለመጠናቀቅ (ይህም ለተጨማሪ ከፍተኛ ወጪ መዳረግ) ከውሳኔ አሰጣጥ ሂደት መጓተት፣ በአሰሪና ተቋራጭ መካከል ቅንጅት ማነስ፣ በአጠቃላይ ከፕሮጀክቶች አስተዳደር የክትትልና ቁጥጥር መላላት ሊመነጭ የሚችል አሳሳቢ ክፍተት ነው።

- የውሎች መቋረጥ እንዲሁም የተቋራጮች መጥፋት መፅደቅ የማይገባቸው ጨረታዎችን ከማፅደቅ ወይም ማሸነፍ የማይገባቸው ተጫራቾች እንዲያሸንፉ ስለሚያደርግ አሳሳቢ ጉዳይ ነው።
- የዋጋ ማስተካከያ በተለያዩ ግንባታዎች ላይ የሚሰጥበት አሰራር ከዕቃዎች የዋጋ መናር አንፃር የመነጨ ሊሆን ቢችልም፣ ከአላግባብ የጥቅም ግንኙነት ጋር ተያይዞ የመምጣት ዕድል ሊኖረው ስለሚችል የሙስና ስጋት ነው ብሎ መደምደም ይቻላል።

## 2.4.10 የኦዲትና ቁጥጥር

ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት በዘረጉ ተቋማት ለሙስና የሚያጋልጡ ብልሹ አሰራሮችና ሙስና በእጅጉ እንደሚቀንስ የተለያዩ ጥናቶች ያሳያሉ። በመሆኑም አንድን ተቋም በሙስና የተጨማለቀ ከሚያደርጉት ነገሮች አንዱ የላላ እና አቅም የሌለው የኦዲት እና ቁጥጥር ቢሮ መኖር ነው። ይህ ቢሮ ወጪዎች በህግ እና ደንብ መፈጸማቸውን በመመርመር ግኝቶችን በማቅረብ ተጠያቂነት እንዲሰፍን ያደርጋል። ጠንካራ የውስጥ ቁጥጥር ሥርዓት ከተዘረጋ ሙስና እንደሚቀንስ እሙን ነው። በተጨማሪም ተቋማት በውጭ አዲተር የፋይናንስ እና ንብረት አስተዳደር አሠራራቸውን የማስገምገም ግዴታ አለባቸው። በግኝቶች ላይም ውይይት፣ እርምት እና ማሻሻያ ማድረግ የግድ ይላቸዋል። ከዚህ አንጻር በዘርፉ ስር ባሉ ሁሉም ተቋማት ውስጥ የኦዲት ሥራ እንደሚሠራ በቅርቡ የተደረገው ጥናት ያሳያል። በዘርፉ ውስጥ ከሚገኙ 18 ተቋማት ውስጥ በ14ቱ የኦዲት ግኝትን መሠረት በማድረግ ማሻሻያዎች እንደሚያደርጉ ጥናቱ አሳይቷል፤ቀሪዎቹ አላደረጉም ወይም አያደርጉም። በተጨማሪ የብሔራዊ ባንክ፣ የመንግስት ኮሙኒኬሽን አገልግሎት፣ የስደተኞችና ተመላሾች አገልግሎት፣ አደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን፣ የአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ እና የኢትዮጵያ ኮሙኒኬሽን ባለስልጣን የኦዲት ሪፖርት ለተገልጋዮች ተደራሽ ስለማድረጋቸው የሚያሳይ መረጃ አለምኖሩ አሳሳቢ ነው።

የዘርፉ ተቋማት ተጋላጭ ሊሆኑ የሚችሉበት ማሳያው ያልተወራረዱ፣ያልተሰበሰቡ እና ያልተከፈሉ ሂሳቦች መኖራቸው ነው።ለምሳሌ፤

- ፌዴራል ፖሊስ ኮሚሽን ሳይወራረዱ የቀሩ ሂሳቦች (ለማሳያነት ያህል የወንጀል መከላከል ጠቅላይ መምሪያ ከብር 7.8 ሚሊዩን በላይ) መኖሩ፣

- በአፍሪካ አመራር ልዕቀት አካዳሚ ከብር 72.2 ሚሊዮን በላይ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ፣ በተጨማሪም ከብር 27.8 ሚሊዮን በላይ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣
- በአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ከብር 1.9 ቢሊዮን በላይ ተሰብሳቢ ሂሳብ መኖሩ
- በፌደራል የሥነምግባርና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን ከብር 5.6 ሚሊዮን በላይ ያልተወራረደ ሂሳብ እና ከብር 8.4 ሚሊዮን በላይ ተከፋይ ሂሳብ መኖሩ፣ በተጨማሪም በድምሩ ከብር 1.06 ሚሊዮን በላይ የተሟላ ማስረጃ ሳይቀርብ ክፍያዎች የተፈፀሙ መሆኑ፣
- በሲቪል ሰርቪስ ኮሚሽን ከብር 4.5 ሚሊዩን በላይ የተሰብሳቢ ሂሳብ ክምችት መኖሩ፣

ክፍተቶች እና የሙስና ስጋቶች

- የኦዲት ግኝቶች ላይ በመመስረት የተወሰዱ ማሻሻያዎች ስለመኖራቸው የሚያሳይ መረጃ ከአራቱ የዘርፉ ተቋማት አልቀረበም፡፡
- በዘርፉ ተቋማት ከፍተኛ መጠን ያለው ያልተወራረደ ሂሳብ መኖሩ የፋይናንስ መመሪያ ጥሰትን እንዲሁም የቁጥጥር ሥርዓት መላላትን አመላካች ስለሆነ አሳሳቢ ስጋት ነው፡፡

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው ጉዳይ ላይ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ፡፡

የተቋማችሁን ኦዲት እና ቁጥጥር ሂደት እንደት ትገመግሙታላችሁ? ሙስናን እና ብልሹ አሰራርን ከመከላከል አንጻር ያለውን ሚና እንደት ይታያል?

### 2.4.11 የግል ጥቅም የሚያጓጓቸው ሀላፊዎች መበራከት

ለሙስና በር ከሚከፍቱ ነገሮች አንዱ የህዝብን ተቋም ተገን አድርገው የግል ጥቅምን የማራመድ ፍላጎት ነው፡፡ የብዙ ተቋማት ሀላፊዎች የተቋማቸወን ራእይ ለስሙ በታፔላ ተጽፎ እንዲቀመጥ ያደርጋሉ እንጅ ዞር በለው አያዩትም፡፡ወንበሯ ላይ ቁጭ የሚሉት የራሳቸውን አላማ ወንበሯን ተጠቅመው እንዴት አድርገው ማሳካት እንደሚችሉ በውስጣቸው እያሰቡ ነው፡፡ከራስ ጥቅም በላይ የሀገርን ጥቅም ማስቀደም እና ነገን ማየት የሚችል አመራር እጅግ አስፈላጊ ነው፡፡ ርእይ ያለው እና የተቋም ርዕይ መሸከም የሚችል አመራር ከሌለ ተቋማት ለሙስና መጋለጣቸው የማይቀር ነው፡፡ ለዚህም ይመስላል የብሄራዊ የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሀላፊዎች ሙስና ውስጥ የተዘፈቁት፡፡ ሙስና በአቋራጭ ለመበልፀግ የሚደረግ የአስተሳሰብ ጉድለት ውጤት ስለሆነ በዚህ አስተሳሰብ የተጠቁ አመራሮች መኖር ተቋማትን ለሙስና ያጋልጣል፡፡ ቁርጠኛ አመራሮች

የሙስናን እና የብልሹ አሰራርን በር ሲዘጉ በአንጻሩ ደግሞ ግድየለሽ እና ራስወዳድ አመራሮች ተቋማቸውን ለሙስና እና ብልሹ አሠራር ዉስጣዊና ዉጫዊ ጥቃት ያጋልጣሉ፤ህዝብንም ያማርራሉ፡፡

## 2.4 በአስተዳደር ዘርፍ አገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች

***የማነቃቂያ ጥያቄ***

- በአግልግሎት አሰጣጥ ዙሪያ ምን ምን አይነት ሙስናዎች እና ብልሹ አሰራሮች ይታያሉ? ተሞክሯችሁን አካፍሉ፡፡

### 2.5.1 የባንክ አገልግሎት አሰጣጥ ብልሽት

የብሄራዊ ባንክ የሚቆጣጠራቸው ባንኮች የድንግቴ ሃብታሞች መፍጠሪያ መሳሪያዎች ከሆኑ ዋል አደር ብለዋል፡፡ "ዛሬ ከፍተኛ መጠን ያለው ገንዘብ በድርድር እንደሚተላለፍ ይሰማል፡፡ ምንና የት እንደሚሰራ የማናውቀው ሰው በአጭር ጊዜ ውስጥ የበርካታ ሰማይ ጠቀስ ፎቆች ባለቤት ሆኖ እናገኘዋለን" እንዲሉ ዶ/ር ጠና ደዎ፡፡

ባንኮች ብዙ ጊዜ ሆን ብለው በሞዳሞድ እና በመደራደር በሀሰተኛ ዶክመንት ሚሊዮን እና ቢሊዮን ብሮችን በማበደር፤አንዳንደ ጊዜ ተጭበርብረው ለምዝበራ እና ሙስና ይጋለጣል፡፡ በመሆኑም ባንኮች ምቹ የሙስና ወንጀል ግዛቶች መሆናቸውን የሚያምልክቱ ጥናቶች ወጥተዋል፡፡ እንድህም ይላል፤ ***'የሙስና ወንጀል በማንኛውም መንግሥታዊ፣ መንግሥታዊ ያልሆኑና በተለያዩ ሕዝባዊ ድርጅቶች የሚፈጸም ቢሆንም ከገንዘብ ዝውውር ጋር ከፍተኛ ትሥሥር ባላቸው በባንኮች፣ በመድኅን ድርጅቶችና መሰል የፋይናንስ ተቋማት ላይ ግን መቆጣጠር በሚያዳግት አኳኋን በከፍተኛ ደረጃ እየተስፋፋ ነው፡፡*** ከ2009 ዓ.ም ወዲህ በተደረገው ዳሰሳ ለዚሁ ጥናት ዓላማ ከ130 በላይ መዛገብት አጥኚ ቡድኑ ምልከታ ያደረገ ሲሆን ከእነዚህ መዛግብት ውስጥ ወደ ሁለት ቢሊዮን ገደማ የገንዘብ ምዝበራ በተለያዩ ባንኮች ላይ ተፈጽሟል፡፡

*ለብልሹ አሰራር ምሳሌ የሚሆን አንድ ነገር እናንሳ፡፡ በ2015 የተደረገ የኦዲት ግኝት እንዳመለከተው በውጭ ምናዛሬ መመሪያን የጣሱ ባንኮች ሰባት መቶ አስር ሺ ዶላር እና ሶስት መቶ ሰባ ሺ ብር የሚያስቀጣቸው ቢሆንም ነገር ግን አርባ አምስት ሺ ዶላር እና ሰልሳ ሺ ብር ብቻ እንድቀጡ ተደርጓል፡፡*

*ባንክ አካባቢ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች*

1. *የውጪ ምንዛሬ ሲጠየቅ ለተባለው ግዥ መዋሉን አለመከታተል፣*
2. *የንግድ ባንኮችን የኦዲት ሪፖርት ለብሄራዊ ባንክ እያደረጉ ስለመሆኑ አለመከታተል፣*
3. *ከላኪዎች ዶላር በትክክል ወደ ሀገር ውስጥ መግባቱን አረጋግጦ በወቅቱ አለማወራረድ*
4. *ባንኮች የሚያቀርቡት የገበያ ዋጋ ማቅረባቸውን የሚያረጋግጥበት የአሰራር ስርዓት አለመኖር ከብዙ በጥቂቱ የብልሹ አሰራር ምልክቶች ናቸው::*

| **የቡድን ውይይት** |
| --- |
| • ውድ ሰልጣኞች በባንክ አገልግሎት አሰጣጥ ሙስና የሚፈጸምባቸውን መንገዶች ዘርዝሩ፤ እንደትስ መከላከል ይቻላል? ተወያዩበት:: |

### 2.5.2 ፓስፖርት አሰጣጥ ጉዳይ

ይህ ተቋም ላለፉት በርካታ አመታት ፓስፖርት አሰጣጥ እና ሌሎች አገልግሎት አሰጣጥ ላይ ባሳየው አፈጻጸም የብልሹ አሰራር ቁንጮ ነው ቢባል ማጋነን አይሆንም:: ለዚህ ማሳያ እንዲሆነን የሚከተለውን ዘገባ እንመልከት፤

*የፓስፖርት አሰጣጥ ውጤታማነትን በተመለከተ በተደረገ ክትትል፤ አገልግሎቱ የመንግስት የባንክ ሂሳብ መክፈትና መዝጋት የገንዘብና ኢኮኖሚ ልማት ስልጣን ሆኖ ሳለ ተቋሙ የራሱን የሂሳብ ቁጥር በኢትዮጵያ ንግድ ባንክ በግለሰቦች ስም ከፍቶ 17.9 ሚልዮን ብር ሰብስቧል:: የተቋሙ ሰራተኞች ከበር ጥበቃ ጀምሮ አስተባባሪዎችና አገልግሎት የሚሰጡ ባለሙያዎች ተገልጋዮችን የሚመቱ ፣ የሚገፈትሩእና አልባሌ ቃላቶችን የሚጠቀሙ መኖራቸውን በክዋኔ ኦዲት ተረጋግጣል ተብሏል (ሸገር FM ሰኔ 2016)::*

*ጥር 3/2016 የፌደራል ስነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ዘገባ እንዳመለከተው በኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት መስሪያ ቤት ከፓስፖርትና ሌሎች አገልግሎቶች አሰጣጥ ጋር በተያያዘ ሲፈፀም በነበረ ስር የሰደደ የሙስና ወንጀል ላይ በተሠራው የሕግ ማስከበር ሥራ ኢትዮጵያውያን ዜጎች ብቻ ማግኘት የሚገባቸውን የኢትዮጵያ ፓስፖርት በሺዎች*

*የሚገመት ዶላርና የኢትዮጵያ ብር በመቀበል ኢትዮጵያዊ ላልሆኑ የውጭ ሀገር ዜጎች ፓስፖርት በመስጠት፣ ከእያንዳንዱ አገልግሎት ፈላጊ ከ10 ሺ ብር እስከ 300 ሺ ብር በማስከፈል ጉዳያቸውን በሕገ-ወጥ መንገድ በመጨረስ ሲሰሩ የነበሩ ሰዎች ላይ ክስ ተመስርቶባቸዋል።*

*ከዚሁ ጋር በተያያዘ ከሕገ-ወጥ ደላሎችና ጉዳይ አስፈፃሚዎች ጋር ትስስር በመፍጠር ለተለያዩ የውጭ ሀገራት ዜጎች እንዲሁም ለትውልደ ኢትዮጵያዊያን በሕገ-ወጥ መንገድ የቱሪስት ቪዛ በማውጣትና በማሳደስ፣ የሃገር ውስጥ የሥራ እና የመኖሪያ ፈቃዶችን በሕገ-ወጥ መንገድ ለውጭ ሃገራት ዜጎች በማውጣት እና በማሳደስ፣ በሕገ-ወጥ መንገድ ሃብት በማፍራት እንዲሁም በሌሎችም ሕገ-ወጥ ድርጊቶች የተጠረጠሩ የኢሚግሬሽንና ዜግነት አገልግሎት ሠራተኞችና ከእነርሱ ጋር የጥቅም ትስስር ያላቸዉ ግለሰቦች ላይ ምርመራ ተጣርቶ በድምሩ 60 ተጠርጣሪዎች ላይ 15 ተደራራቢ ክሶች የቀረቡ ሲሆን በሌሎች 6 መዝገቦች ላይም በተመሳሳይ ክስ መመስረቱን መረጃው ያመለክታል።*

***የቡድን ውይይት***

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው የሙስና ጉዳይ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

*ተቋማችሁ ለእንደዚህ አይነት ሁኔታ ተጋላጭ የሚሆንበት ክፍተቶችን ዘርዝሩ?*

በአስተዳድር ዘርፍ ውስጥ የሚገኙ ተቃማት ውስጥ ሰልጣኞች ወደፊት ልብ ብለው የሚታገላቸው በርካት ብልሹ አሰራሮች አሉ። ለምሳሌ ተቋሙን ለለቀቁ ሰራተኞች ስራ ገበታ ላይ እንዳሉ አድርጎ ደመወዝ መክፈል፣ ተሿሚ ላልሆኑ ሰዎች የወንበር ጥቅማጥቅም መክፈል፣ ለግል ጉዳያቸው ወደተለያዩ ቦታዎች ለሚሄዱ ሰራተኞች ውሎ አበል መክፈል፣በሚሊዮን የሚቆጠር ገንዘብ በወቅቱ አለማወራረድ፣ ተቋሙ የሰው ሀይል እጥረት ሳይኖረብተ ሰራተኞች መቅጠር እና ማዛወር እና ህግን ሳይከተሉ ደመወዝ ማስተካከል ከብዙ በጥቂቱ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች ናቸው።

### 2.5.3 የተንዛዛ አሰራር

በሀገራችን የሚገኙ ተቋማትም አብዛኛውን ጊዜ የሚሰጡት አገልግሎት ግልጽነት የጎደለው፣ ተገቢውን ጥራት ያላሟላ እና ፍጥነት የሚጎድላቸው ናቸው። አገልግሎት ፈላጊው ዜጋ የሚፈልገውን አገልግሎት ለማግኘት ወደ ተቋም ሲሄድ የሚፈልገው አገልግሎት የት እንደሚገኝ፣

አገልግሎቱን ለማግኘት ምን ማሟላት እንዳለበት፣አገልግሎቱን ማን እንደሚሰጠው፣ ለአገልግሎቱ ምን ያህል ክፍያ እንደሚፈጽም ማወቅ ይፈልጋል፡፡

- የኢንቨስትመንት ማበረታቻ አሰጣጥ
- የኢንቨስትመንት ፈቃድና ምዝገባ አሰጣጥ
- ለኢንቨስተሮች ድጋፍና ክትትል አሰጣጥ

በሀገራችን ውስጥ ባለው የንግድ እና ኢንቨስትመንት ምዝገባ ሥርዓት ውስጥ ትልቁ ፈተና አንድ ሰው ንግድ ለመጀመር ወይም ኢንቨስት ለማድረግ የሚያስችለውን ፈቃድ እና የምስክር ወረቀት ለማግኘት ያለው መዘግየት ነው፡፡ ለሚፈልጉት እና ላጎረሳቸው ከነፋስ ፈጥነው ፈቃድ ይሰጣሉ፤ ለማይፈልጉት ደግሞ አሳር ያሳያሉ፡፡

**በኢንቨስትመንት ኮሚሽን አካባቢ የሚታዩ ብልሹ አሰራሮች፤**

- ፈቃድ በሰጣቸው ኢንቨስተሮች ላይ በየወቅቱ ክትትል እና ድጋፍ አለማድረግ፣
- ለኢንቨስተሮች ምቹ ሁነታ አለመፍጠር፣
- ኢንቨስተሮች ያዝመዘገቡትን ካፒታል አለማርጋገጥ እና ማስርጃ አለመያዝ።

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች ከታች በቀረበው ናሙና ላይ ውይይት አድርጋችሁ የተቋማችሁን ልምድ ጨምራችሁ ውጤቱን አቅርቡ፤

በ 2015 ዓም በተደረገ ጥናት በአስተዳደር ዘርፍ ስር ከሚገኙት 18 ተቋማት መካከል ለሙስና ተጋላጭ የሆኑ የስራ ክፍሎችን አሰራር በተመለከተ የሙስና ስጋት ጥናት ያካሄዱት ስድስቱ ብቻ ናቸው:: በመሆኑም ተቋማቱ እንዴት ለሙስና እንደሚጋለጡ አብራሩ:: ተቋማችሁም ከዚህ አኳያ ያለበት አቋም ምን ላይ እንድሆነ አስረዱ::

### 2.5.4 በቂ ያልሆነ ቁጥጥር እና ተጠያቂነት

ውጤታማ ቁጥጥር ማነስ፡- በቂ ያልሆነ የክትትልና የቁጥጥር ዘዴዎች ቁጥጥር ያልተደረገበት ሙስና ያስከትላል:: የቁጥጥር እና ክትትል ስርዓቶች ካልተዘረጉ ብልሹ አሰራሮች በቀላሉ ሳይስተዋል ይቀራል:: ከዚህ በተጨማሪም የጸረ-ሙስና እርምጃዎች ደካማ አፈፃፀም መሆኑ ለሙስና በር ይከፍታል፡፡ ይህም ማለት የፀረ-ሙስና ህጎች እና ፖሊሲዎች ቢኖሩም እንኳን ደካማ

የማስፈጸሚያ ሂደት ውጤታማነትን ይቀንሳል። ይህም በቂ ያልሆነ ምርመራ እና የሙስና ድርጊቶችን ለፍርድ ማቅረብን ይጨምራል።

### 2.5.5 ፖለቲካዊ ተጽእኖ እና በትዉዉቅ የሚሰሩ ስራዎች

የፖለቲካ ጣልቃ-ገብነትን በመፍጠር የፖለቲካ ሰዎች በአስተዳደር ዘርፍ ውስጥ ወዳጆችን፣ ቤተሰብን ወይም አጋሮችን ለመጥቀም ያላቸውን ተጽዕኖ ሊጠቀሙበት ይችላሉ፣ ይህም እንደ ዘመድ ወይም በሌሎች የአሰራር ግንኙነቶች አድልዎ ወደ መሳሰሉ ልማዶች በማምራት የፖለቲካ ጣልቃ-ገብነትን ይፈጥራል ይህም ለሙስና ሊያጋልጥ ይችላል። በተጨማሪም የሙስና ኔትወርኮች መዘርጋት ሌላው የሙስና መንስኤ ሊሆን ይችላል። ይህም ማለት ሙስና በፖለቲካ፣ በቢዝነስ እና በአስተዳደራዊ ዘርፎች በተዘረጋ ኔትወርኮች ውስጥ ስር ሰድዶ ችግሩን ለመፍታት እና ለማጥፋት አስቸጋሪ ያደርገዋል።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሁለት በአስተዳር ዘርፍ የሚስተዋሉ የሙስና ስጋቶች፣ተጋላጭነት እና ብልሹ አሰራሮችን የተዳሰሱ ሲሆን በዚህም ምዕራፍ ውስጥ በተነሱ ነጥቦች ላይ ሠልጣኞች ተገቢውን ግንዛቤ እና ክህሎት እንዳገኙ ይታመናል። የሙስና ስጋት እና ተጋላጭነት በአንድ ተቋም ውስጥ የሚታዩ ሙስናን ለመፈጸም ምቹ ሁኔታ የሚፈጥሩ አሰራሮች ማለት ነው። ስጋት እና ተጋላጭነቶች በጊዜ ካልታረሙ አንድ ተቋም የተመሰረተበትን አላማ ከግብ እንዳያደርስ አሉታዊ ተጽዕኖ ያሳድራሉ። በተቋማት ውስጥ ለተለያዩ የብልሹ አሰራሮች መኖራቸው ለሙስና የመጋለጥ እድላቸውን ከፍ ያደርገዋል።

በአገልግሎት አሰጣጥ ላይ የሚፈጸሙ አንዳንድ ሙስና ዓይነቶች የሕዝብ አገልግሎት እኩል ተጠቃሚነት ሰብዓዊ መብትን ይገፋሉ፣ እንዲሁም የዜጎችን ተደራሽነት የሚጥሱ እና መሠረታዊም መብቶችን በመጋፋት ኢ- ፍትሃዊነትን ያባብሳሉ። ከዚህም በላይ የሙስና መንሰራፋት የአገልግሎት አሰጣጡን ሰንሰለት መበላሸት ሊያስከትል ስለሚችል የመንግሥት መዋቅር ዜጎቹን የመጠበቅ ግዴታውን መወጣት እንዳይችል ያደርጋል።በዚህም የተንሳ የአገልግሎት አሰጣጡ እጅግ አስመራሪ እና ተስፋ አስቆራጭ እየሆነ ነው። በአሁኑ ወቅት ዜጎች ያለ እጅ መንሻ በየትኛውም መሥሪያ ቤት ወይም ተቋም የትኛውንም ጉዳይ ማስፈጸም አይቻልም ብለው አምነው ተቀብለዋል።

በሚገባ ያልተደራጀ የስነ ምግባር እና ጸረ ሙስና ቢሮ መኖር፣ ጠንካራ የኦዲት ቢሮ አለመኖር፣ የግልጽነት መጥፋት፣ ብቃት ያለው የሰው ሀብት አስተዳደር አለመኖር፣ የተዝረከረከ ግዥ እና ንብረት አስተዳደር መኖር ተቋማትን ለሙስና የሚያጋልጡ ሁኔታዎች ናቸው። ከዚህ አንጻር የባንክ አገልግሎት አሰጣጥ ብልሽትና ግልጽነት የጎደለው የተንዛዛ አሰራር በዋናናት ተለይተዋል። ስለሆነም የምዕራፉን ዓለማዎች መሰረት በማድረግ ሰልጣኞች የአገልግሎት ዘርፉ እንዴት ለሙስና ሊጋለጥ እደሚችል መለየት ችለዋል እንዲሁም ተግልጋዮች ላይ የሚደርሰውን እንግልት በመረዳት በየተቋማቸው ጥሩ አገልጋይ ለመሆን የሚያስችል እውቀት እና ክህሎት አግኝተዋል ተብሎ ይታመናል።

## የምዕራፍ ሁለት ማጠቃለያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡

1. ከስልጠናው ባገኛችሁት ግንዛቤ መስረት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት እንደት እንደሚፈጠር አስረዱ?
2. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ለሙስናና ብልሹ አሰራር ተጋጭ የሚያድርጉ አሰራሮችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ።
3. በምትሰሩበት ተቋም ውስጥ ከበድ ላለ ሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነት የሚታይበት የስራ ክፍል የትኛው ነው? ለምን?
4. በተቋማች ውስጥ ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ተጋላጭነትን ለመቀነስ የተሰሩ ስራዎችን ዘርዝሩ እና ለተሳታፊዎች አስረዱ።

## ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሁለት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለማሳየት (√) ምልክት በማስቀመጥ ምን ያህል እንደተረዳችሁ አሳዩ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ጥያቄዎች | የማመሳከሪያ ነጥቦች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
| 1 | ሙስና በማንኛውም ተቋም ውስጥ ሊከሰት እንደሚችል ተረድቻለሁ | | | | |
| 2 | ለሙስና ተጋላጭነት የአሰራር ክፍቶች ጋር ቁርኝት ያለው መሆኑን ተረድቻለሁ | | | | |
| 3 | የክትትል እና የቁጥጥር ተቋማት መላላት ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳት መተንተን ችያለሁ | | | | |
| 4 | ለሙስና ተጋላጭነት የሚያመጡ ሁኔታዎችን ተረድቻለሁ | | | | |
| 5 | በተቋማችን ውስጥ ከዝቅተኛ እስከ ከፍተኛ ያሉ የሙስና ስጋቶች በሚገባ መገንዘብ ችያለሁ | | | | |
| 6 | ተጠያቂነትን ለማስፈን የደንቦች መዘጋጀት አስፈላጊ መሆኑን ተገንዝቤያለሁ | | | | |
| 7 | በተቀማችን ውስጥ ያሉ ለሙስና የሚያጋልጡ አሰራሮችን ለይቻለሁ | | | | |
| 8 | የብልሹ አሰራርን ምንነት አእና ምንጭ ተረድቻለሁ | | | | |
| 9 | በአስተዳድር ዘርፍ ብልሹ አሰራር የዜጎችን መብት እንደሚጋፋ ተገንዝቤያለሁ | | | | |

# ምዕራፍ ሶስት፦ በአስተዳደር ዘርፍ የሚስተዋሉ ሙስና እና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች

## 3.1 የምዕራፍ ሶስት መግቢያ

የተለያዩ የጥናትና ምርምር ግኝቶች እንደሚያመለክቱት ሙስና ዘርፈ ብዙ የሆኑ ጉዳቶችን በማድረስ አብዛኛውን ህዝብ ለከፋ ድህነት ከመዳረግ አልፎ የሰውን ልጅ ህልውና የሚፈታተን አደጋ ነው። ሙስና የአደገኛ የጦር መሳሪያዎችና አደንዛዥ እጾች ዝውውር እንዲስፋፋ፣ የተፈጥሮ ሚዛን እንዲቃወስ አልፎ ተርፎም ሰላም፣ ፀጥታና ፍትህ አደጋ ላይ እንዲወድቁ የሚያደርግ ማህበራዊ ጠንቅ ነው። ሙስና በአገር ላይ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችንና ቀውሶችን ያስከትላል።

ከዘመኑ ጋር እየተለዋወጠ፣ጉዳቱም ከፍተኛ እየሆነ የመጣው ሙስናን ለመከላከል ጠንካራ ስልቶችን መቀየስ በጣም ያስፈልጋል። ተለዋጭ ባህሪ ያለውን ሙስና ለመዋጋት ዘርፎች እንደየተቋማቸው ባህርይ በየጊዜው የሚሻሻል፣ መጠነ ሰፊ ጉዳዮችን የሚዳስስ የሙስና መከላከልያ ስትራቴጂዎችን መንደፍ ይጠበቅባቸዋል። ሙስናን የመከላከል ተግባር ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው። ሙስናና ብልሹ አሰራርን በመከላከል በሙስናና ብልሹ አሰራር ምክንያት ይባክን የነበረውን ሃብት በመታደግ ያለውን  ሃገራዊ ሃብት ለታለመለት ሥራ ለማዋል ያስችላል።

ሙስና እንዲከሰት የሚያደርጉ ሁኔታዎችን መከላከል ላይ ለምሳሌ አመለካከት፣አጋጣሚ (ምቹ ሁኔታ) ከባብያዊ እና ማህበራዊ ግፊት ላይ መስራት ያስፈልጋል። ችግሩ ከተከሰተ በኋላም የችግሩን ፈጣሪ እና የባከነውን ሃብት ለማፈላለግና ለማግኘት የሚባክነውን ተጨማሪ ወጪ ያስቀራል፤ በመንግስት ተቋማት ለሙስናና ብልሹ አሰራር ክፍተት የማይፈጥር ጠንካራ የአሰራር ሥርዓት እንዲፈጠር ያደርጋል። በዚህ ምእራፍ ውስጥ በዘርፉ ውስጥ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስልቶች ይዳሰሳሉ።

## 3.2 የምዕራፍ ሶስት ዓላማዎች

ሠልጣኞች ከዚህ ስልጠና በኋላ

- የሙስናን ዘርፈ ብዙ ጉዳቶች ጉዳቶችን ይለያሉ፣
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ይተነትናሉ፣
- የሙስና መከላከያ ስልቶችን ያወዳድራሉ፣
- በዘርፉ ውስጥ ያሉ የመከላከለያ ስልቶች ይዘረዝራሉ፣
- የዘርፋቸውን የሙስና መከላከያ ስልቶች ይገመግማሉ፣
- በዘርፋቸው የመከላከያ ስልቶችን ይተገብራሉ፣

**የማሰልጠኛ ዘዴዎች፡-** የአእምሮን ጓዳ ማንኳኳት/Brain storming፣ገለፃ፣ጥያቄና መልስ፣ ውይይት፣አስረጅ ናሙና (case study)

**የሚወስደው ጊዜ፡-** 4:00

**መርጃ መሳሪያዎች፡-** ፍሊፕ ቻርት፣ማርከር፣ፓወር ፖይንት፣ የተዘጋጀ ሰነድ

## 3.3 በአስተዳደር ዘርፍ ሙስና የሚያስከትላቸው ጉዳቶች

የሙስና ጉዳት ዘርፈ ብዙ መሆኑን አይተናል፡፡ ነገር ግን በዋናነት ሙስና በአንድ አገር ላይ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊ እና ከባቢያዊ ጉዳት ያደርሳል፡፡ እንዘህን ጉዳቶች በዝርዝር ከዚህ ቀጥሎ እናያቸዋልን፡፡ እነዚህን ጉዳቶች በዝርዝር ከማየታችን በፊት በቅድሚ ከዚህ በታች የቀረበውን ኬዝ በማየት ውይይት አድርጉበትና ውጤቱን አቅርቡ፡፡

**ኬዝ ሰባት፡ በዲሞክራቲክ ኮንጎ ሲመረቅ የተደረመሰው ድልድይ**

- በማዕከላዊ አፍሪካ የምትገኘው ዲሞክራቲክ ኮንጎ በዋና ከተማዋ ኪንሳሻ ከፍተኛ ወጪ በማውጣት ለእግረኞች ድልድል የተሰራ ሲሆን የከተማዋ ሹማምንቶች ተሰራ የተባለውን ድልድል ለመመረቅ በቆሙበት ድልድዩ ተደርምሶ ፈርሷል፡፡ የምረቃው ስነስርዓት ቪዲኦ ሊንክ እዚህ ተያይዟል (https://youtu.be/hlk_GcRI6LM)፡፡
- ውድ ሰልጣኞች ከላይ የቀረበውን ኬዝ መነሻ በማድረግ እንደዚህ አይት ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉትን ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊ፣ ፖለቲካዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችን በመወያየት አቅርቡ



1. **ኢኮኖሚያዊ ጉዳቶች**

በአለም አቀፍ ደረጃ ሙስና ከፍተኛ የሆነ የኢኮኖሚ ቀውስ እንደሚያስከትል በርካታ ጥናቶች አረጋግጠዋል ይህ ደግሞ በማደግ ላይ ባሉ ሀገራት የከፋ ነው፡፡ ሙስና ኢኮኖሚያዊ ቀውስ በመፍጠር የአገር ልማት እንዲቀጭጭ፣ የኢኮኖሚ እድገት እንዲገታ፣ ኪሣራና ውድቀት እንዲፋጠን እና ድህነት በከፍተኛ ደረጃ እንዲስፋፋ በማድረግ ዜጎች ወደ ከፋ የኑሮ አዘቅት ውስጥ እንዱወድቁ ያደርጋል፡፡

እንዳት ያደርጋል ብለን ከጠየቅን ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ማስረጃዎች/ማብራሪያዎች ማየት ይቻላል

- ለኢኮኖሚ እድገት የተነደፉ የልማት ፕሮጀክቶች ለህብረተሰቡ የጎላ ጥቅም በማይሰጡ ፕሮጀክቶች እንዲተኩ በማድረግ፣
- የመንግስት በጀት ለተገቢው እና ቅድሚያ ሊሰጠው በሚገባው ተግባር እንዳይውል በጥቂቶች ለሚፈልጉት ተግባር እንዲውል በማድረግ፣
- ከፍተኛ የውጪ ኢንቨስተሮችን /ባለሃብቶችን/ ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያስችል አገልግሎቶችን ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ በመጠየቅ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያደርጉትን ተሳትፎና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በመገደብ፣

- የአገርን ሃብት ጥቂት ባለስልጣናትና ባለሃብቶች እንዲቀራመቱት ሁኔታዎችን በማመቻቸት አብዛኛውን ህዝብ ለድህነት፣ ለችግርና ለከፋ የጉስቁልና ኑሮ በመዳረግ፣
- ለህዝብ የሚቀርቡ የፍጆታ ዕቃዎች መጠንና ጥራትን በመቀነስ የግብይትን ዋጋ በከፍተኛ ሁኔታ በማናር ህዝብን ለከፋ የኢኮኖሚ ችግር ይዳርጋል፡፡

## 2. ማህበራዊ ጉዳቶች

ሙስና ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ እንደሚያስከትል እሙን ነው፡፡ ሙስና በህዝቦች ዘንድ የሞራል ውድቀት፣ የሥነምግባር ቀውስ እና የሕግ የበላይነት እንዲይሰፍን በማድረግ ከፍተኛ የሆነ ማህበራዊ ቀውስ /ሥራ አጥነት፣ ጎዳና ተዳዳሪነት፣ ዋልጌነት፣ ጥፋተኛነትና ሥርዓተ አልበኝነት፣ ሴተኛ አዳሪነተ ወዘተ/ ያስከትላል፡፡

እንደዚህ አይነቶች ማህበራዊ ቀውስ እንዳት ሊከሰቱ እንደሚችሉ ለመረዳት ከዚህ በታች የቀረቡትን ዝርዝር ማብራሪያዎች ማየቱ ጥሩ ነው

- ሙስና በሰፈነበት አገር በዋነኛነት ሰፊው ህብረተሰብ የችግሩ ተጠቂ በመሆኑ በሚያጋጥመው የኢኮኖሚ ቀውስ ሳቢያ አብዛኛው ህዝብ ለድህነት ይዳረጋል፡፡ ሰርቼ የተሻለ ኑሮ አኖራለሁ ብሎ የሚመኘው ህዝብ ለሥራ አጥነት፣ ለጎዳና ተዳዳሪነት እና ለሴተኛ አዳሪነት ይጋለጣል፣ እጅግ ሲከፋም ለስደት እንዲዳረግ ምክንያት ይሆናሌ፡፡
- በሙስና ሰበብ ለማህበራዊ አገልግሎት ለትምህርትና ለልዩ ልዩ አገልግሎት ሰጪ ተቋማት ግንባታ መዋል የሚገባው የመንግስት ሃብት ለጥቂቶች እንዲውሉ ስለሚያደርግ፣ አብዛኛው ህብረተሰብ የመሠረተ ልማት ተጠቃሚ መሆን አይችልም፡፡ የትምህርት እድል የንጹህ ውሃ አቅርቦትና በቂ የህክምና አገልግሎት በማጣት ለመሃይምነት፣ ለኋላ ቀርነት እና ለከፍተኛ የጤና ችግር ይጋለጣል፡፡

## 3. ፖለቲካዊ ጉዳቶች

ሙስና ከፍተኛ የሆነ ፖለቲካዊ ችግር ያመጣል፡፡ ሙስና ህዝብ በመንግስትና በሕግ የበላይነት ላይ አመኔታ እንዲያጣና በዲሞክራሲ ሥርዓት ላይ ጥርጣሬ እንዲኖረው በማድረግ ፖለቲካዊ አለመረጋጋት እንዲሰፍን ያደርጋል፡፡

ሙስና ከላይ የተዘረዘሩትን ዋና ዋና ፖለቲካዊ እንዴት ሊያመጣ እንደሚችል ከዚህ በታች የተዘረዘሩትን ምሳሌዎች ማየት አስፈላጊ ነው

- የመንግስት ሥራዎች ከተገቢው አሰራርና ከሕግ ውጪ እንዲከናወኑ በማድረግ፣
- ሙስና ዜጎች በሀገራቸው ብሔራዊ ሃብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው ስለሚጋብዝ ህዝቦች በመንግስት ላይ የሚኖራቸው እምነት እንዲሸረሸርና በሚኖሩበት ሀገር ውስጥ የቤተኝነት ስሜት እንዳይሰማቸው በማድረግና በዚህም የተነሳ በመንግስትና በህዝብ ዘንድ ትልቅ ክፍተት እንዲፈጠር ያደርጋል፣
- በአንድ አገር ውስጥ የፖለቲካ መረጋጋት እንዲጠፋ በማድረግ ነፃና ፍትሀዊ ምርጫ እንዳይኖር በማድረግ ለህገ ወጥ ሹም ሽር እንዲጋለጥ ምክንያት ይሆናል፣

### 4. ከባቢያዊ ጉዳቶች

ሙስና የስግብግብነት ስሜትን አግንኖ ስለሚያወጣ የተፈጥሮ ሚዛንን በማዛባት ከባቢያዊ ሁኔታዎችን የሚያዛቡ ተግባሮችን በመፈጸም የሰውን ልጅ የመኖር ህልውና የሚፈታተኑ ጉዳቶችን ያስከትላል።

ሙስና እንዳት ከባቢያዊ ችግር እንደሚፈጥር ከዚህ በታች የተቀመጡትን ሁለት ነጥቦች በዝርዝር ማጤን ያስፈልጋል

- የተፈጥሮ ሃብቶች ከማንኛውም ሃብት ባልተናነሰ መልኩ ለሙስና የተጋለጡ ናቸው። ይህም በሁለት መንገድ ሲሆን አንደኛው የተፈጥሮ ሃብቶችን ኃላፊነት በጎደለው መንገድ መመዝበር ነው። ሁለተኛው ደግሞ ለአካባቢ ብክለት ከፍተኛ ሚና የሚኖራቸውን፣ የአካባቢ ዑደትን ሊያዛቡ የሚችሉ አደገኛ የኬሚካል ተረፈ ምርቶችን በየብስ፣ በአየርና በምድር ላይ ማስወገድን የመሳሰሉት ይገኙበታል።
- ከህገ ወጥ የመሬት ወረራ ጋር ተያይዞ ከተሞች ማስተር ፕላናቸውን ጠብቀው ለልማትና ለዕድገት አመቺ የሆነ አሰፋፈር እንዳይኖራቸው በማድረግ በከተሞች እድገት ላይ አለታዊ ተጽእኖ ያሳድራል።

ጠቅለል ባለ መልኩ ከአስተዳር ዘርፍ ተጨባጭ ሁኔታ አንጻር ሙስና እና ብልሹ አሰራር የሚከተሉት ዋና ዋና ጉዳቶች ይኖሩታል

- ከፍተኛ የውጪ ኢንቨስተሮችን /ባለሀብቶች;ን/ ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያስችል አገልሎቶችን ለማግኘት ጉቦ እንዲከፍሉ በመጠየቅ ወደ አገር ውስጥ ገብተው ገንዘብና እውቀታቸውን በአገር ኢኮኖሚ እድገትና ልማት ላይ ለማዋል የሚያደርጉትን ተሳትፎና የኢንቨስትመንት እንቅስቃሴን በመገደብ አኮኖሚያዊ ጉዳት ያስከትላል
- የመንግስት ሥራዎች ከተገቢው አሰራርና ከሕግ ውጪ እንዲከናወኑ በማድረግ ዜጎች ለአላስፈላጊ እንግልትና ወጪ እንዲዳረጉ በማድረግ የመልካም አስተዳደር ችግር እንዲፈጠር ያደርጋል
- በተቋም ውስጥ ሥነምግባር መጓደል እና ብልሹ አሰራር መንሰራፋት በሰራተኞች መካከል መተማመንና መተባበር እንዳይኖር ያደርጋል
- በፖሉስ ተቋም የተወሰኑ ወንጀሎች ክትትል እንዲይደረግባቸው፣ ወይም በተመረጡ የወንጀለ ተሳታፉዎች ላይ ብቻ ክትትል እንዲደረግ በማድረግ፣ የተደራጀ ወንጀል (ለምሳሌ አደገኛ እጽ ማዘዋወር ወንጀል) ወይም ሌሎች ህገወጥ ተግባራቶች ሪፖርት እንዳየደደረጉና እንዲደበቁ በማድረግ፣ ምስክሮችን በማስፈራራት እንዳይመሰክሩ ወይም እውነቱን እንዳይናገሩ በማድረግ፣ የሀሰት የተቀነባበሩ ማስረጃዎችን በማዘጋጀት፣ የተያዙ የኮንትሮባንድ እቃዎችን በመሰወርና መልሶ በመሸጥ የመሳሰለትን በመፈጸም የህግ የበላይነት እንዳይሰፍን ያደርጋል ይህም በመንግስትና በህዝብ መካከል መተማመን እንዳይኖር ያደርጋል
- ኢፍትሃዊ በሆነ አስተዳደር የሰራተኛውን እድገት፣ ቅጥርና ጥቅማ ጥቅም ችሎታን መሰረት ባደረገ መንገድ ባለማከናወንና የሰራተኛውን የስራ ፍላጎትና ሞራል እጅጉን እንዲጎዳና ምርታማነት እንዲቀንስ ያደርጋል፡፡
- ዜጎች በሀገራቸው ሀብት ተጠቃሚ እንዳይሆኑ፣ የተዛባ የሀብት ክፍፍል እንዲፈጠር፣ መብታቸው እንዲነካና አድሎ እንዲፈጸምባቸው፣ በመንግስት ላይ የሚኖራቸው እምነት እንዲሸረሸርና፣ በመንግስትና በህዝብ ዘንድ ትልቅ ክፍተት እንዲፈጠር አስተዋጽኦ በማበርከት የፖለቲካ አለመረጋጋት ያጋልጣል፡፡
- በመረጃና ደህንነት አገልግሎት በጥቅም በመተሳሰርና የግል ፍላጎትን በማስቀደም የሀገርን ሚስጥራዊ የደህንነት መረጃዎች ለሶስተኛ ወገን አሳልፎ በመስጠት የሀገር ሉዐላዊነት እንዲደፈርና የፖለቲካ አለመረጋጋት እነዲፈጠር ያደርጋል፡፡

## 3.4 በዘርፉ የሚስተዋሉ የሙስና እና ብልሹ አሰራሮች መከላከያ መንገዶች እና ስልቶች

**የማነቃቂያ ጥያቄዎች፤**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች አንብቡና ከጎናችሁ ተሳታፊ ጋር በመሆን ተወያዩና የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡፡

1. የምታውቋቸውን የሙስና እና የብልሹ አሰራሮች መከላከያ ስልቶችና ጥቅማቸውን ዘርዝሩ፡፡
2. በዘርፋችሁ ተግባራዊ የሚደረጉ ጠንካራ የሙስና መከላከያ ስልቶች ዘርዝሩ፡፡
3. ሙስናና ብልሹ አሰራርን አስቀድሞ መከላከል የሚያስገኘውን ፋይዳ አብራሩ፡፡
4. ሙስናን የመከላከል ሃላፊነት የማን ነው ብላችሁ ታስባላችሁ?
5. ሙስናን ባንከላከለው ምን ጉዳት የሚያስከትል ይመስላችኋል፡፡

### 1. የዘርፉን የሰው ሃይል ማጎልበት

ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የዘርፉን የሰው ሃይል በእውቀት፣ በክህሎት እና በአመለካከት መገንባት ዋነኛው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ ሰራተኞች የተቋማቸውን ራእይና ተልእኮ እንዲሁም እሴት ጠንቀቀው ሊያውቁ ይገባል፡፡ ተቋማቸው የሚሰራባቸውን የህግ ማእቀፎች የስራ መመሪያዎችና ደንቦችን ማወቅ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በእጅጉ ይረዳል፡፡ በተለይ ሰራተኞች ስራቸውን ስነ-ምግባርን የተላበሰ አገልግሎት እንዲሰጡ ለማድረግ በሥነ-ምግባራር ጉዳይ ላይ አመለካከትን የሚቀርጹ የስነ-ምግባር ስልጠናዎችን በየጊዜው መስጠት ተገቢ ነው፡፡ ሙያዊ ብቃታቸውንም እንዲያጎለብቱ ሙያዊ ስነ-ምግባርን የሚያሻሽሉ ስልጠናዎች ሊዘጋጁ ይገባል፡፡ ለጠቅላይ ሚ/ረ ተጠሪ በሆኑ ተቋማት ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ራሳቸውን ጸረ ሙስና አርበኛ አድርገው መመልከት ይጠበቅባቸዋል፡፡

**የቡድን ውይይት**

*የአደጋ ስጋት ስራ አመራር ኮሚሽን ሃላፊዎች ከአንድ የግል ድርጅት ጋር በመመሳጠር በተረጂዎች ስም ለእርዳታ የተዘጋጀን ምግብና ምግብ ነክ ያልሆኑ ቁሶች አላግባብ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸዋል፡፡*

*በተቋማችሁ የዚህ አይነት ሙስና እንዳይፈጸም ከተፈጸመም እርምት እንዲወሰድ ምን ታደርጋላችሁ?*

## 2. ግልጽነትና ተጠያቂነት ማስፈን

### 2.1 ግልጽነት

የግልጽነት ጉዳይ ትክክለኛና ወቅታዊ መረጃን ለዜጎች የማድረስ ጉዳይ ነው። ዜጎች ወቅታዊና ትክክለኛ መረጃ ማግኘት ከቻሉ አሰራሮች ሁሉ ግልጽ ስለሚሆኑ ለአስተዳደር በደል፣ ለብልሹ አሰራር ወይም ለሙስና ሰለባ አይሆኑም።

ዘርፎች በሴክተሩ የሚሰጠውን መንግስታዊ አገልግሎት በተመለከተ ምን ዓይነት አገልግሎት፣ በምን መስፈርት፣ ለማን እንደሚሰጥ በዝርዝር የሚያብራራ መመሪያ ማውጣትና ተጠቃሚው ህብረተሰብ ይህንኑ በሚገባ እንዲያውቅ ማድረግ ይኖርባቸዋል።

በመንግስት አሰራር ውስጥ የግልጽነት አሰራር ከሌለ ዜጎች የሚፈልገውን መረጃ በሚፈልገው ወቅትና መጠን ሊያገኝ አይችልም። ይህ ደግሞ መብቱን ለመጠየቅና ለማስከበር እንቅፋት ከመፍጠሩም ባሻገር ፈጻሚውን አካል ተጠያቂ ማድረግ አይችልም።ስለሆነም በየተቋማቸው ግልጽነት እና ተጠያቂነት እንድሰፍን መታገል ያስፈልጋል። ከሰው ሀይል ቅጥር እስክ ግዥ አፈጸም ያሉ ተግባራት እና ውሳኔዎች ግልጽ እንድሆኑ ከፍተኛ ጥረት ማድረግ። ግልጽነትን ተግባራዊ የማድረግ ሂደት ጊዜና ትግል የሚጠይቅ ቢሆንም በምንም ሊተካ የማይችል አስፈላጊ ተግባር ነው።

### 2.2 ተጠያቂነት

የተጠያቂነት አሰራር ማለት ስራውን የሚሰራው አካል ስራውን በአግባቡ መስራት እንዳለበት እና እንዲሰራ የተሰጠውን ኃላፊነት በአግባቡ ካልተወጣ፣ ለፈፀመው ጥፋት የሚጠየቅበት /በቅጣት ወይም ካሳ በመክፈል/ ስርአት ማለት ነው። ይህ እውን እንዲሆን ግን የሚጠይቅ ማለትም ስራህን በአግባቡ ሰርተሀል ወይም አልሰራህም በማለት ለመከታተል፣ ለመቆጣጠርና እንደሚፈለገው ሆኖ ሳይገኝ ሲቀር ኃላፊነትን መወጣት በውስጥ ያሉ አሰራሮች፣ ደንቦችና እሴቶችን ባግባቡ ተግባራዊ ማድረግ ሲሆን፣ ተጠያቂነት ደግሞ ለውጭ ጠያቂ አካል ምላሽ መስጠት ላይ ትኩረት ያደርጋል፡ ፡ ተጠያቂነት ተግባራዊ ከሚሆኑበት መንገዶች መካከል የተሰሩ ስራዎችን በተመለከተ፣ ለህግ አውጪው አካል፣ በየደረጃው ላሉ ሃላፊዎች ሪፖርት ማቅረብ፣ ለሚነሱ ጥያቄዎች ምላሽ መስጠት፤ ተጠያቂነት መንግስት የሚሰጠውን ስራ ባግባቡ በመስራት፣ ህብረተሰብን ለማገልገል

ፈቃደኛ በመሆንም ይገለጻል፡፡ከዚህ አንጻር ሙስናን መከላከል ላይ ትኩረት ተደርጎ መሰራት ያለበት ቢሆንም ጠበቅ ያለ ርምጃ መውሰድንም ይጠይቃልይ፡፡

## 3 የሥነ-ምግባር ደንብን ተግባራዊ ማድረግ

በሙስና መከላከል ስትራቴጂ ውስጥ ሙስናን ለመከላከል ከሚጠቀሱ ዘዴዎች መካከል አንዱ የሥነ-ምግባር ደንብ አዘጋጅቶ ተግባራዊ ማድረግ ነው፡፡ በአንድ ተቋም ውስጥ የሥነ-ምግባር ደንብ መኖሩ በተቋሙ ውስጥ ተቀባይነት ያለው የሥነ-ምግባር ደረጃ እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ የተቋሙ ሪሶርስ(ሃብት) ባግባቡ ጥቅም ላይ እንዲውል፣ አድሎዊነት እንዲወገድ፣ ቅንነትና ታማኝነት እንዲሰፍን ይረዳል፡፡ በተጨማሪም ግልጽነትና ተጠያቂነት እንዲኖር፣ የተሰጠን ሃላፊነትም ባግባቡ ለመወጣት የሥነ-ምግባር ደንብ አስፈላጊ መሳሪያ ነው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንብ ማንኛውም ስራ ሲሰራ ሥነ-ምግባርን በተላበሰ መልኩ መሆን እንዳለበት ስለሚደነግግ ለሙስና እና ለብልሹ አሰራር የሚያጋልጡ የሥነ-ምግባር ባህርያትን ለመግታት ትልቅ አስተዋጽ አለው፡፡ የሥነ-ምግባር ደንቡን ተግባራዊ በማድረግ ረገድ ሁሉም ሰራተኛ ተሳታፊ የሚሆንበትን መንገድ መቀየስም ተገቢ ነው፡፡ በመጨረሻም ለሚከሰቱ የሥነ-ምግባር መተላለፎችን አግባብ ላለው አካል እንዲጠቁሙ ማድረግ፣ በመጠቆማቸውም ምክንያት መገለል እና ሌሎች ጥቃቶች እንዳይደርስባቸው መከላከል ይገባል፡፡

## 4 የሃብትና ጥቅም ማሳወቅና ማስመዝገብ

በየዘርፉ ሊከሰት የሚችለውን ሙስናና ብልሹ አሰራር ለመከላከልና ተጠያቂነትን ለማስፈን ከሚጠቅሙ የመከላከያ ስትራቴጂዎች መካከል በዘርፉ ውስጥ ያሉ ሰራተኞችና የስራ ሃላፊዎች ሃብታቸውን እንዲያሳውቁና እንዲያስመዘግቡ  ማድረግ አንዱ ነው፡፡ የሃብት ማሳወቅና ምዝገባ ሕጋዊና ትክክለኛ የሥራ ፍሬ የሆነን ሃብት ምንጬ ካልታወቀ ሀብት ለመለየት ያስችላል፡፡ ከዚህ ባሻገር ውሳኔ ሰጪዎች ውሳኔ በሚሰጡበት ጊዜ በጥቅም ግጭት ሙስና ውስጥ እንዳይገቡ ያግዛል፡፡

## 5. የጥቅም ግጭትን የሚፈጥሩ ሁኔታዎችን መከላከል

የጥቅም ግጭት (Conflict of interest) ከመንግስት ወይም ከህዝብ ተሰጠውን ሃላፊነት ባግባቡ እንዲወጣ አደራ የተሰጠው የስራ ሃላፊ ወይም ባለስልጣን በስራ ተግባር እና ሃላፊነቱ ዉስጥ ከህዝብ፣ ከመንግስትና ከሃገር ጥቅም ይልቅ የግሉን፤ የቤተሰቡን ወይም የራሱን የቅርብ ዘመዱን

የገንዘብ ወይም ማንኛውም ሌላ ጥቅም የማስቀደም ሁኔታ ሲያጋጥም ወይም ከመንግስታዊ ስራ ወይም ኃላፊነት ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ ግጭት ሊፈጥር የሚችል ሁኔታ ነው፡፡

የጥቅም ግጭት ማንኛውም ዓይነት ኃላፊነትና ስልጣን ባለበት ሁኔታዎች እና አካባቢ ውስጥ እንደሚኖር ይታመናል፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ውስጥ ያሉ የስራ ሃላፊዎችና ሰራተኞች ለዜጎች አገልግሎት በሚሰጡበት ወቅት ከሃላፊነታቸው ጋር በቀጥታ ወይም በተዘዋዋሪ መንገድ የጥቅም ግጭት ውስጥ ሊከታቸው የሚችሉ ሁኔታዎች ሲያጋጥማቸው ግጭቱን በመከላከል ወይም ባግባቡ ማስተዳደር የሚችሉበትን ስልት ሊቀይሱ ይገባል፡፡

ለምሳሌ በተቋማት ለጥቅም ግጭት ሊፈጥሩ የሚችሉ አሠራሮችንና አደረጃጀቶችን በጥናት መለየትና የጥቅም ግጭት እንዳይከሰት ለመከላከል የሚያስችል አሰራርን መዘርጋት፣ ሲፈጠርም አፋጣኝ እርምጃ መውሰድ ይገባል፡፡

## 6. የዘርፉን የፀረ-ሙስና ሚና ሚንስትሪም/የስራ አካል ማድረግ

የጸረ-ሙስና ትግል የአንድ ሰሞን ወይም የዘመቻ ስራ አይደለም፡፡ ዘርፎች ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ቁርጠኛ መሆን ይጠበቅባቸዋል፡፡ ቁርጠኝነታቸው ከሚገለጽባቸው መንገዶች መካከል የጸረ-ሙስና ሚናን የስራቸው አካል ወይም ሜይንስትሪም ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ይህም ሲባል ዘርፎች የጸረ-ሙስና ትግልን የእቅዳቸውና፣ የየእለት የስራ እንቅስቃሴያቸው፣ የሪፖርትና የውጤት ግምገማ አካላቸው ሊያደርጉት ይገባል ማለት ነው፡፡ የተቋሙ ማህበረሰብም በተደራጀና በተቀናጀ መልኩ የሚያደርጉትን የጸረ-ሙስና እንቅስቃሴ በባለቤትነት ስሜት ላይ በመመስረት ተሳትፏቸውን ከፍ ሊያደርጉ ይገባል፡፡ ከዚህ አንፃር እያንዳንዱ ተቋም ሙስናን ለመከላከልና ለመዋጋት የሚረዳው አደረጃጀት ፈጥሮ ወደ ትግሉ በቁርጠኝነት እንዲገባ ያግዘው ዘንድ የሥነ-ምግባር መከታተያ ክፍሎችን ማጠናከር ይጠበቅበታል፡፡

## 7. የመንግስት የስራ ሃላፊዎች ሚናን ማጠናከር

የተቋማት የስራ መሪዎች በተቋማቸ ሙሽናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ግንባር ቀደም መሆናቸው ይታወቃል፡፡ ከዚህ አኳያ በየተቋሙ ያሉ የስራ ሃላፊዎች ራሳቸውን የመልካም ስነ-ምግባር አርዓያ ከማድረግ ጀምሮ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል በርካታ ተግባራት ይጠበቅባቸዋል፡፡ ከነዚህም መካከል፡-

- በተቋም ውስጥ ሥነ-ምግባራዊ አመራርን ተግባራዊ ማድረግ፣
- ሙስናን የመከላከል ስራን በተቋም ውስጥ ሜይንስትሪም ማድረግ፣
- ሥነ-ምግባራዊ ባህል በተቋም ውስጥ እንዲሰፍን ማድረግ፣
- የጥቅም ግጭትን የመከላከያ ስትራቴጂዎችን ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ፣
- የአገልግሎት አሰጣጥ ስታንደርድን እንዲወጣ እና ተግባራዊ እንዲደረግ ማድረግ፣
- በተቋሙ የአሰራር ስርዓት እንዲተገበር ለሙስና በር የሚከፍቱ አሰራሮችን ማሻሻል፣
- በስነ-ምግባራቸው የላቁና በአገልግሎታቸው የተመሰገኑ ሰራተኞችን እውቅና መስጠት፣

## 8. ከባለድርሻ አካላት ጋር በትብብርና በቅንጅት መስራት

በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሥነ-ምግባርን ማስፈንና ሙስናን መከላከል ለዘርፉ ብቻ የሚተው እንቅስቀሴ ሳይሆን የባለድሻ አካላትንም ንቁ ተሳትፎ የሚጠይቅ ነው፡፡ ምክንያቱም ባለድርሻን ያላሳተፈ የፀረ-ሙስና እንቅስቃሴ ረጅም ርቀት መጓዝ አይችልምና ነው፡፡ ከዚህ አኳያ ህብረተሰቡ በዘርፉ የሚከሰቱ ሙስናና ኢ-ስነምግባራዊ ድርጊቶችን በማጋለጥ ሃላፊነታቸውን እንዲወጡ ማድረግ የሚችሉበትን ሁኔታዎች ማመቻቸት ይገባል፡፡ እንዲሁም ዘርፎች ግልጽነትና ተጠያቂነትን ለማስፈን በዚህ ዙሪያ ከሚሰሩ የሲቪል ማህበራትና የሙያ ማህበራት ጋር በቅንጅትና በትብብር ሊሰሩ ይገባል፡፡

## 9. ቴክኖሎጂን ጥቅም ላይ ማዋል

በአገልግሎት አሰጣጥ ሂደት ተገልጋዮችን ለሙስና የሚያጋልጥ እንግልትን ለማስቀረት ቴክኖሎጂን ተግባራዊ ማድረግ ጠቃሚ ነው፡፡ ቴክኖሎጂ ለሙስና የሚያጋልጥ የተንዛዛ ቢሮክራሲን በማሳጠርና ቀልጣፋ አገልግሎት እውን እንዲሆን በማድረግና ተግባራት ከሰዎች ንክኪ ነጻ እንዲሆኑ በማድረግ ሙስናና ብልሹ አሰራርን ለመከላከል ወቅቱ የሚጠይቀው የመከላከያ ስልት ነው፡፡ በመሆኑም በዘርፉ ያሉ ሰራተኞች ሙስናን መከላከል የሚያስችል የቴክኖሎጂ ፈጠራዎችን በመስራት፣ ራሳቸውን ለአዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ዝግጁ በማድረግ በቴክኖሎጂ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ሃላፊነታቸውን ሊወጡ ይገባል፡፡

ከላይ ከጠቀሱት በተጨማሪም የሚከተሉት አይነተኛ ሙስናን የመከላከያ ስልቶች ናቸው፣

- ጥቆማ መስጠት

- ስራን በወቅቱ ና ሰአት ሳይሸራርፉ መስራት
- የአገልጋይነት ባህል ማዳበር እና ሃገርን መውደድ
- ሀብትን ማሳውቅ እና ማስመዝገብ
- የሙስናን ባህል በሀቀኝነት እና ታታሪነት መቀየር፡፡ ሙስና ማህራዊ እና ባህላዊ መሰረት ስለአለው እሱን መቀየር፤ የፀረ ሙስና የባህል አብዮት ማቀጣጠል፤
- በየተቋማቸው የሚጠረጠሩ ሙሰኞች ካሉ መካታተል፣ማጋለጥ፡፡ የተቋሙ መመዝበር የኔ ቤት መመዝበር ነው ብሎ ማመን ያስፈልጋል፡፡

## 3.5 ማጠቃለያ

በምዕራፍ ሶስት በአስተዳዳር ዘርፍ ለሚከሰቱ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች የሚያስከትሉት ጉዳት እና መከላከያ ስልቶች በዝርዝር ታይተዋል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ በዋናት ሙስናና ብልሹ አሰራር በሀገር ኢኮኖሚ ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት፣ በህዝብና መንግስት መካከል የሚፈጥረውን አለመተማመን እንዲሁም የዜጉችን ማህበራዊ ኑሮ ምን ያህል እንደሚያቃውስ እና መከላከያ መንገዶችን ለመዳሰስ ተሞክሯል፡፡

በዚህ ምዕራፍ እንደተመላከተው መከላከል ማለት አንድ ሁኔታ ወይም ችግር ከመፈጠሩ በፊት ወይም ተፈጥሮም ከሆነ ሰፋ ያለ ጉዳት ከማድረሱ በፊት አስፈላጊ እርምጃዎችን በመውሰድ ችግሩ በመፈጠሩ ይደርስ የነበረውን ጉዳት ሙሉ በሙሉ እንዳይፈጠር ማድረግ ወይም የጉዳቱን መጠን ዝቅተኛ እንዲሆን ማድረግ ነው፡፡ ሙስናና ብልሹ አሰራርን የመከላከል ተግባርም በአንድ ዘርፍ ሙስናና ብልሹ አሰራሮች ሊያስከትሉ የሚችሉትን ከፍተኛ የሆነ ኢኮኖሚያዊ፣ ማህበራዊና ፖለቲካዊ ኪሳራ ለማስቀረት ወይም ለመቀነስ በሚያስችል መልኩ የችግሩን ምንጭ የማድረቅ ተግባር ነው፡፡ በአንድ ዘርፍ ውስጥ ሊከሰቱ የሚችሉ የሙስናና የብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችል ብቸኛና ወጥ የሆነ የመከላከያ ሥልት የለም፡፡ ይሁንና እንደተቋሙ ባህሪና ተልዕኮ እንዲሁም በየጊዜው የሚለዋወጠውን የሙስና ስትራቴጂ ግምት ውስጥ ያስገባ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂ ነድፎ ተግባራዊ ማድረግ ይገባል፡፡ በዚህ ምዕራፍ ውስጥ የሙስና እና ብልሹ አሰራርን ተግባራዊ ለማድረግ የሚያስችሉ ዘጠኝ ስትራቴጂዎች ተመላክተዋል፡፡ ይሁንና የመከላከያ ስልቶቹ ዘጠኝ ብቻ ናቸው ማለት እንዳልሆነ ሰልጣኞች ልብ ሊሉ ይገባል፡፡ ልምዳቸውንና እውቀታቸውን በመጠቀም ልዩ ልዩ የሙስና መከላከያ ስትራቴጂዎችን በማምጣት የበኩላቸውን ሃላፊነት ሊወጡ ይገባል፡፡

**የማጠቃለያ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች የቀረቡትን ጥያቄዎች በቡድን ተወያይታችሁ የደረሳችሁበትን ለተሳታፊዎች አቅርቡ፡

1. በዚህ ስልጠና ከተመለከታችኋቸው የመከላከያ ስልቶች መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ የተደረጉት የትኞቹ ናቸው? የተገኘውስ ለውጥ ምንድን ነው?
2. በዚህ ስልጠና ውስጥ ከተመለከታችሁት የመከላከያ ስትራቴጂ መካከል በዘርፋችሁ ተግባራዊ ያልተደረጉት የትኞቹ ናቸው? ምክንያታችሁን አስረዱ፡፡
3. ከምትሰሩበት የስራ አካባቢ አንጻር ቴክኖሎጂን በመጠቀም ሙስናና ብልሹ አሰራርን እንዴት መቀነስ እንደሚቻል በዝርዝር ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡
4. በዚህ ስልጠና ካያችኋቸው በተጨማሪ ሙስናና ብልሹ አሰራርን መከላከል የሚያስችሉ ስትራቴጂዎችን ዘርዝሩና ለተሳታፊዎች አስረዱ፡፡

**ራስን መገምገሚያ ጥያቄዎች**

ከዚህ በታች በምዕራፍ ሶስት የቀረበውን ትምህርት ምን ያህል እንደተረዳችሁ የምታመሳክሩበት ሰንጠረዥ ቀርቧል፡፡ በዚሁ መሰረት በእያንዳንዱ የማመሳከሪያ ነጥብ ትይዩ ምን ያህል እንደተረዳችሁ ለማሳየት (√) ምልክት በማስቀመጥ ምን ያህል እንደተረዳችሁ አሳዩ፡፡

| ተ.ቁ | የማመሳከሪያ ጥያቄዎች | የማመሳከሪያ ነጥቦች | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ከፍተኛ |
| 1 | ዋናዋና የሙስና መካለከያ ስልቶችን ለይቻለሁ | | | | |
| 2 | ሙስናን እና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል የሚያስችል ዕውቀት እና ክህሎት አግኝቻልሁ | | | | |
| 3 | በምሰራበት ተቀም በቂ የሆነ ሙስናን ለመከላከል የሚያስችሉ አሰራሮች እንደሚያስፈልጉ ተድቻለሁ | | | | |
| 4 | ግልጽነት እና ተጠያቂነት ሙስናን ለመዋጋት ያላቸውን ሚና ማስረዳት እችላለሁ | | | | |
| 5 | በትብብር ሙስናን በመዋጋት ረገድ ያላቸውን ሚና መተንተን እችላለሁ | | | | |
| 6 | ሙስናን ለመከላከል የወጡ ዋና ዋና ህጎችን አውቃልሁ | | | | |

# የሞጁሉ ማጠቃለያ

የሙስና ጉዳት የሀገርን ህልውና እስከመፈታተን ይደርሳል፡፡ ለተለያዩ ወንጀሎች መበራከት ሙስና ከፍተኛውን ድርሻ የሚወስድ እንደሆነ ይታወቃል፡፡ እጅግ ከፍተኛ የሆኑ ኢኮኖሚያዊ፣ ፖለቲካዊ፣ ማህበራዊና ከባቢያዊ ጉዳቶችንና ቀውሶችን እንደሚያስከትል በርካታ የጥናትና ምርምር ግኝቶች ያሳያሉ፡፡ በዚህ የማሰልጠኛ ሞጁል የሙስና ምንነት፣የሙስና ወንጀል ዝርዝሮች እና አይነቶች፣ በአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ የሚስተዋሉ የሙስና ተጋላጭነት፣ስጋት እና ብልሹ አሰራሮች፣ጉዳቶች እና መከላከያ ስልቶች በስፋት ታይተዋል፡፡ ስልጠናውን ተጨባጭ ለማድረግም የተለያዩ አስረጅ ናሙናዎች ቀርበዋል፡፡ ሙስና እጅግ በጣም እየሰፋ፣ከዘመኑ ጋር ተለዋዋጭ ባህሪ እየያዘ እና ጉዳቱም በሀገር እና ህዝብ ላይ ከፍ እያለ ስለመጣ ምንቱን አውቆ ለመከላከል ትጋት እና ቁርጠኝነት ማሳየት ያስፈልጋል፡፡በዚሁ ሂደትም ሙስና ብልሹ አሰራሮችን ለመከላከል አንድ ወጥ የሆነ ስልት ስለሌ ተቋማት እንደተጋላጭነታቸው የራሳቸውን ስልት መቀየስ ያስፈልጋቸዋል፡፡የሙስና መፈጸሚያ ስልቱ እየረቀቀ ስለሆነ የረቀቀ መከላከያ ስልት ያስፈልገዋል፡፡ መከላከል ሲባል የሙስና እና ብልሹ አሰራር ምንጮችን ማድረቅ ማለት ሲሆን፤ከተከሰተ በኋላም አስተማሪ እርምጃ መውሰድ ማለት ነው፡፡ የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ለሙስና እና ብልሹ አሰራር ያላቸው ተጋላጭነት እና መከላከያ መንገዶች እና ስልቶችን ሰልጣኞች አውቀው ለመከላከል ዝግጁ እንድሆኑ ይህ ስልጠና አእገዛ እንደሚያደርግ ይታመናል፡፡

## አባሪ 1፡- ቅድመ እና ድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት

ከዚህ በታች ያለው የቅድመ እና ድህረ ስልጠና ቼክ ሊስት በዋናናት ትኩረት የሚያደርገው በአስተዳር ዘርፍ ባሉ ተቋማት ውስጥ የሚታዩ ሙስናና ብልሹ አሰራሮችን በተመለከተ ሠልጣኞች ስልጠናውን ከመውሰዳቸው በፊትና ስልጠናውን ከወሰዱ በኋላ ያላቸውን የግንዛቤ ደረጃና ልዩነት ለመለካት ነው፡፡

ሀ). ሰልጣኞች በዚህ ቼክ ሊስት የተዘረዘሩትን ሃሳቦች ስልጠና ከመጀመራቸው በፊት እንዲሁም ስልጠናውን ካጠናቀቁ በኋላ እንዲሞሉት እና ጥያቂዎቹን እንዲሰሩ ይጠበቃል፡፡

ለ). በቁጥሮች ትይዩ ባለት ሳጥኖች ውስጥ የ‹‹X›› ምልክት በማድረግ ምላሻችሁን አስቀምጡ፡፡

**ቅድመ ስልጠና መገምገሚያ ቼክ ሊስት**

| ተ ቁ | ርዕስ ጉዳይ | በርዕሰ ጉዳዩ ላይ ያለ የግንዛቤ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | የሙስና ምንነት ላይ ያለ እውቀት እና አመለካከት | | | | |
| 2 | የሙስና ምክንያቶችን በተመለከት ያለው እውቀት | | | | |
| 3 | የሙስና አይነቶች ላይ ዕውቀት እና ግንዛቤ ደረጃን በተመለከተ | | | | |
| 4 | የሙስና መገለጫዎች ላይ ዕውቀት እና ግንዛቤ | | | | |
| 5 | የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ለሙስና ያላቸው ተጋላጭነት በተመለከተ | | | | |
| 6 | የሙስና ተጋላጭነት ላይ ያለ ዕውቀት እና ክህሎት | | | | |
| 7 | በአስተዳደር ዘርፍ የሚታየውን የሙስና ተጋላጭነትን መቀነስ ስለመቻሉ በተመለከተ | | | | |
| 8 | ሙስና በአስተዳደር ዘርፍ ላይ ያስከተለው ጉዳትን በተመለከት | | | | |
| 9 | የሙስና መከላከያ ላይ ያለ ግንዛቤ እና አመለካከት | | | | |

## ድህረ ስልጠና መገምገሚያ ቼክ ሊስት

| ተ ቁ | ርዕስ ጉዳይ | በርዕስ ጉዳዩ ላይ ያለ የግንዛቤ ደረጃ | | | |
|---|---|---|---|---|---|
| | | ዝቅተኛ | መካከለኛ | ከፍተኛ | በጣም ዝቅተኛ |
| 1 | ስልጠናውን ከወሰዱ በኂላ ሙስና ምንነት ላይ ያገኙት እውቀት | | | | |
| 2 | የሙስና ምክንያቶችን በተመለከት ያገኙት እውቀት | | | | |
| 3 | ከስልጠናው በሙስና አይነቶች ላይ ያገኙት ዕውቀት እና ግንዛቤ ደረጃን በተመለከተ | | | | |
| 4 | በአስተዳደር ዘርፍ የሚታዩ የሙስና መገለጫዎች ላይ ያገኙት ዕውቀት እና ግንዛቤ | | | | |
| 5 | የአስተዳደር ዘርፍ ተቋማት ምን ያህል ለሙስና ተጋላጭ መሆናቸውን ያገኙት ግንዛቤ በተመለከተ | | | | |
| 6 | ከስልጠናው በኂላ በአጠቃላይ የሙስና ተጋላጭነት ላይ ያገኙት ዕውቀት እና ክህሎት | | | | |
| 7 | ሙስና በአስተዳደር ዘርፍ ላይ ያስከተለውንና ወደፊትም ሊያስከትል የሚችለውን ጉዳትን በተመለከተ ከስልጠናው በኂላ ያገኙት ግንዛቤ | | | | |
| 8 | ከስልጠናው በኂላ የሙስና መከላከያ ላይ ያለ ያገኙት ግንዛቤ | | | | |
| 9 | በአጠቃላይ ሙስና በማህበረሰቡና ኢኮኖሚው ላይ ሊስከትል የሚችለውን ጉዳትና ቀውስ በተመለከተ ያገኙት እውቀትና ግንዛቤ | | | | |
| 10 | ስልጠናው በአስተዳር ዘርፍ የሚታዩ ሙስናንና ብልሹ አሰራርን ከመዋጋት አንጻር ያለው ሚና | | | | |

**ለ. የሚከተሉት ጥያቆች ላይ ማብራሪያ እና ትንታኔ ይስጡ፤**

1. በአስዳደር ዘርፍ ተቋማት ውስጥ ሙስና እንዴት እንድሚፈጸም ያብራሩ?
2. የሙስና ዋናው ምንጭ ምን ይመስላችኋል?
3. የሙስና ተጋልጭነትን እንዴት ይገልጹታል?
4. ሙስና የሚያስከትለውን ጉዳት ያብራሩ
5. ሙስናን ለመከላከል ምን መደረግ አለበት ይላሉ?
6. የስልጠናውን አስፈላጊነት እንዴት ይገልጹታል? በቂ እውቀት እና ክህሎት አግኝቻለሁ ብለው ያምናሉ ወይም አግኝተዋል?
7. በስልጠናው ውስጥ ወደፊት መካተት አለበት ብለው የሚምኑት ርዕስ ጉዳይ ካለ በዝርዝር ቢያስቀምጡ?

# አባሪ 2፡ በዘርፉ የተገኙ ኬዞች

## ኬዝ ሁለት፡ የክብሪቷ ታሪክ

ውድ ሰልጣኞች ይህንን ኬዝ አንብባችሁ ከታች ለተቀመጡ ጥያቄዎች ምላሻችሁን አስቀምጡ፤

*በአንዱ መስሪያ ቤት የተከሰተ ሁነት ነው፡፡ ድርጅቱ በአምራች ዘርፍ የተሰማራ ሲሆን የግብርና ምርቶችን በፋብሪካ አቀነባብሮ ወደ ውጪ ይልካል፤ለሀገር ውስጥ ገበያም ያቀርባል፡፡ ተረፈ ምርቶችን ለማስወገድ የጽዳት ዕቃዎች ግዥ ለመፈጸም ጨረታ አወጣ፡፡ በዚህ መሰረት አንድ የፅዳት ዕቃዎች አቅራቢ ንግድ ድርጅት ክብሪት ለማቅረብ አሸናፊ ሆኗል፡፡ ውሉ ላይ እንደተገለፀው የሚቀርበው ክብሪት መለኪያው ፓኬት ሲሆን መጠኑም አንድ ሺ ፓኬት ነው ይላል፡፡*

*ፓኬት የሚለው አገላለፅ አሻሚ ስለሆነ የግዥ ክፍል ማብራሪያ እንዲሰጥ ተጠይቆ የክብሪት መለኪያው አንድ ፓኬት አስር ፍሬ ክብሪት የሚይዝ መሆኑ ይገልጻል፡፡ በዚህ መሰረት ድርጅቱ ማቅረብ ያለበት 10000 (አስር ሺ) ክብሪት ነው ማለት ነው፡፡ ነገር ግን ድርጅቱ ገቢ ያደረገው 1000 (አንድ እሺ ፍሬ) ክብሪቶችን ነው፡፡ ዘጠኝ ሺህ ክብሪት አላስገባም፡፡ የድርጅቱ ወኪል ነኝ ያሉ ግለሰብም አንድ ፓኬት ክብሪት ማለት አንድ ፍሬ ክብሪት ነው የሚል ምላሽ ሠጥተዋል፡፡ የንብረት ክፍል ባለሙያ አንድ ፓኬት ክብሪት ማለት አንድ ፍሬ ክብሪት ማለት ነው፤ የሚታወቀውም በዚህ መልኩ ነው የሚል ሀሳብ አንፀባርቀዋል፡፡ በተለይ ውሉ ላይ አንድ ፓኬት ክብሪት ማለት አስር ፍሬ ክብሪት የሚይዝ ማለት ነው ተብሎ በግልፅ ስላልተቀመጠ ለውዝግብ መነሻ ሁኗል፡፡ ድርጅቱ አንድ ፍሬ ክብሪት በወቅቱ 7.60 ብር (ሰባት ብር ከስልሳ ሳንቲም ዝቅተኛ ዋጋ በማቅረባቸው አሸናፊ እንደሆኑ ውሉ ያመለክታል)፡፡ ስለሆነም የድርጅቱ ተወካይ እንደሚሉት ጨረታ ስለሆነ ገበያ ላይ በአንድ ብር የምትሸጠዋን አንድ ፍሬ ክብሪት በ7.60 በማሸነፍ አቅርቧል፡*

1. ከዚህ ነገር ጀርባ ሙስና የተፈጸመ ይመስላችሁል ወይ?
2. ጥፋተኛው ማነው?
3. በተቋማችሁስ የዚህ አይነት ሁኔታ ገጥሟችሁ ያውቅ ከሆነ ለተሳታፊዎች አካፍሏቸው፡፡

## ኬዝ ሶስት፡ የቡድን ውይይት

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ፡፡

በብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ውስጥ በሃላፊነት ቦታ እና በግዥ ባለሙያነት የሚሰሩ መካከለኛ አመራሮች የፈጸሙት ነው፡፡ ተቋሙ የግዥ ፍላጎተ ሳይኖረው፣ጥያቄ ሳይቀርብ እና ከተቋሙ ዕውቅና ውጪ ለተቋሙ ነው በማለት ከተለያዩ ፋብሪካዎች የገዙትን ሲሚንቶ ለግለሰቦች በመሸጥ ከሰላሳ ሚሊዮን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸው ወደ ማረሚያ ቤትም ወርደዋል (ጸረ ሙስና ድጅታል ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 6 እና 7/2015፤ገጽ፣2)፡፡

ይህ ተቋም ለዚህ አይነቱ ሙስና እንዴት ተጋላጭ ሊሆን እንደቻለ አብራሩ፡፡**ኬዝ ሶስት፡ የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ፡፡

በብሄራዊ መረጃ እና ደህንነት አገልግሎት ውስጥ በሃላፊነት ቦታ እና በግዥ ባለሙያነት የሚሰሩ መካከለኛ አመራሮች የፈጸሙት ነው፡፡ ተቋሙ የግዥ ፍላጎተ ሳይኖረው፣ጥያቄ ሳይቀርብ እና ከተቋሙ ዕውቅና ውጪ ለተቋሙ ነው በማለት ከተለያዩ ፋብሪካዎች የገዙትን ሲሚንቶ ለግለሰቦች በመሸጥ ከሰላሳ ሚሊዮን ብር በላይ ለግል ጥቅማቸው አውለዋል የሚል ክስ ቀርቦባቸው ወደ ማረሚያ ቤትም ወርደዋል (ጸረ ሙስና ድጅታል ጋዜጣ ቅጽ 1 ቁጥር 6 እና 7/2015፤ገጽ፣2)፡፡

ይህ ተቋም ለዚህ አይነቱ ሙስና እንዴት ተጋላጭ ሊሆን እንደቻለ አብራሩ፡፡

**ኬዝ አራት፤ የሽፍጥ ውድድር**

ውድ ሰልጣኞች በቀረበው ናሙና ላይ ውይይት አድርጋችሁ የተቋማችሁን ልምድ ጨምራችሁ ውጤቱን አቅርቡ፤

አንድ አዲስ አበባ ውስጥ የሚገኝ ተቋም ለስምንት ቦታዎች ሰራተኞችን አወዳድሮ ለመመደብ ማስታወቂያ ያወጣል፡፡ አመልካቾች በማስታወቂያው መሰረት ማስረጃቸውን ያስገባሉ፡፡በሂደት ላይ እንዳለ ክፍት ቦታዎቹ ስምንት ሳይሆኑ አስራ አንድ መሆናቸው መረጃ አፈትልኮ ወጣ፡፡ ከዚያ በኋላ ትርምስ ተፈጠረ፤ ሶስቱ ቦታ ላይ ካለ ውድድር የሚፈልጉትን ሰው ሊያስቀምጡ ነበር ማለት ነው፡፡

➢ ይህ ከምን የመጣ ይመስላችኋል?

➢ ተጋላጭነቱ በምን ምክንያት ተፈጠረ?

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

ለጠቅላይ ሚ/ር ጽ/ቤት ተጠሪ ከሆኑ ተቋማት አንዱ ለሁለት ህንጻ ግንባታ ጨረታ አውጥቶ ካወዳደረ እና አሸናፊው ተለይቶ ስራ ከተጀመረ በኋላ አሸናፊው ድርጅት ጥሩ ስለሆነ በሚል ሰበብ አምስት ህንጻዎችን እንዲገነባ መስጠት የሙስና ድርጊት ነው ወይስ አይደለም? ከዚህ ጉዳይ ጀርባ እነማን ያልተገባ ጥቅም የሚያገኙ ይመስላችኋል?

**የቡድን ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

የግልጽነት እና ተጠያቂነት አስፈላጊነት ላይ እና አለመኖራቸው የሚያስከትለው ጉዳት ምንድን ነው? እንዴትስ ከተጋላጭነት ጋር ይያያዛል።

**ኬዝ አምስት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

**የአገልግሎት ሰጪና ተቀባይ ወግ**

*አንዳንድ ጊዜ ተገልጋይ ለመንግስት ሰራተኛ ወይም ሀላፊ ስጦታ የሚሰጠው ፈልጎ ሳይሆን፣ አገልግሎት ሰጪው ይህንን ካላድረግክልኝ አገልግሎቱን አላቀርብልህም በማለቱ ሊሆን ይችላል።ይህ ሁኔታ የሚያሳየው ተገልጋይ የሆነው ሰው ከመንግስት ወይም ህዝባዊ ድርጅት ሰራተኛው የማይገባ አገልግሎት እንዲሰጠው አልጠየቀም። ነገር ግን መብቱ የሆነው ነገር ብቻ እንዲፈጸምለት ነው የሚጠይቀው። ይሁንና የመንግስት ሰራተኛው አገልግሎቱን ለማግኘት ጥቅም ካልሰጠው በስተቀር የማይፍጸምለት ከሆነ ይህ ተገልጋይ ይህንን በህግ መብቱ የሆነውን ነገር አገልግሎት ለማግኘት ስልጣንን በእጁ ሊያዘው ሰው በመክፈሉ ለምን በወንጀል ተጠያቂ እንዲሆን*

ይድረጋል? እንደዚህ አይነት ሁኔታ የምትሰሩበት ተቋም ለእንድዚህ አይነት ሁኔታ ተጋላጭ ሊሆን የሚችልበትን ሁኔታ አብራሩ?

**የጥንድ ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

ስዎች አገልግሎት በሚያገኙበት ወቅት አገልግሎት ሰጪው ሳይጠይቅ አገልግሎት ፈላጊው በኢኮኖሚ የተሻልን ስለሆን በሚል ለሃላፊው የሻይ ቢሰጡት ሃላፊውን ያስጠይቀዋል ወይ?

**የጥንድ ውይይት**

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

ስዎች አገልግሎት በሚያገኙበት ወቅት አገልግሎት ሰጪው ሳይጠይቅ አገልግሎት ፈላጊው በኢኮኖሚ የተሻልን ስለሆን በሚል ለሃላፊው የሻይ ቢሰጡት ሃላፊውን ያስጠይቀዋል ወይ?

## ኬዝ ስድስት

ውድ ሰልጣኞች የሚከተለው አስገራሚ የሙስና ጉዳይ ላይ ጠለቅ ያለ ውይይት አድረጋችሁ ውጤቱን አቅርቡ።

የ2015 ኦዲት ሪፖርት እንደሚያመለክተው አንድ የውጪ ሀገር ባለሀብት ከትውልደ ኢትዮጵያውያን ጋር ከ200 ሺህ ዶላር በላይ በሚሆን ካፒታል ኢንቨስት ለማድረግ ፈቃድ ወስዷል። ነገር ግን ከ150 ሺ በላይ ካፒታሉ አልተመዝገበም። ይህ ጉዳይ የሙስና አመላካች ሊሆን ይችላል ወይ? ከሆነስ እንደት?

## ዋቢ መጽሐፍት / References

Kato, Damian (1995) Enhancing of ethics, Transparency and Accountability in Uganda. Workshop on civil service reform in Anglophone Africa. Cape Town (Unpublished).

Klitgaard,Robert(1988)Controllingcorruption.UniversityofCaliforniapress.Berkeley.

Stapenhurst, Rick and shar. J.K punden (ed). (1999) curbing corruption To word 73 a model for Building national Integrity. EDI development studies: World Bank, Washington D.C.

Stapenhusrt Rick and shahrzad, sedigh. (1999) "An overview of the cost of corruption and strategies to Deal withit." In Rick stapcnhurs and sahr J. kepunden (ed.) curbing corruption:Tp word a model for Building national Integrity. EDI development studies, World Bank,WashingtonD.C.

Transparency International. (2008) "Where does corruption Flourish" TI source Book. TI,Berlin. (1995) "Building a global coalition against corruption" annual Report. IL, Berlin.(2002) Global corruption Report TL,Berlin.

World Bank (2006) Corruption and Economic Development: Helping countries combat corruption The Role of the World Bank. Washington D.C (1999) Curbing corruption. Economic Development Institute of the World Bank, Washington D.C.

World Bank (2006) Diagnising Corruption inEthiopia, Perceptions, Realities, and the Way Forward for Key Sectors, Library of Congress Cataloging-in-Publication Data, WashingtonD.C.

የፌደራል የሥነምግባር እና የፀረ-ሙስና ኮሚሽን
FEDERAL ETHICS AND ANTI-CORRUPTION COMMISSION

ስልክ;- +251115-52-77-85/+251115-53-69-01
ፖሳቁ P.O.Box :- 34798/99
ኢ-ሜይል:- E-mail FeaccEthiopia2013@et
ፌስቡክ/www.facebook.com/feaccOfficial
ድረ-ገጽ/ www.feacc.gov.et